# የወንጌላዊ ኬዳሞ የአገልግሎት ስጦታዎች

## "የማገለግለው ስለሚከፈለኝ ዋጋ ሳይሆን አስቀድሞ ስለተከፈለልኝ ታላቅ ዋጋ ነው" ወ/ዊ ኬዳሞ ሜቻቶ

*ወንጌላዊ ኬዳሞ 88 ዓመታትን ባስቆጠረችው ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የቤተ ክርስቲያኒቱን እኩያ እድሜ ኖረው ከ65 ዓመታት በላይ አገልግለውባታል። በእነዚሁ ሰባት አስርት ዓመታትም በብዙ መስኮች እግዚአብሔር በሰጣቸው ጸጋ ሲያገለግሉ ኖረዋል። በቤተ ክርስቲያኒቱ መዋቅር ከአጥቢያ ወንጌላዊነት እስከ አገር አቀፍ ብሔራዊ የወንጌላውያን አሠልጣኝ ወንጌላዊነት፣ በመጀመሪያ ካገለገሉባት የማር ክዳን ከለበሰች አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ተነስተው በታላላቅ እና ታሪካዊ የአሜሪካ፣ የካናዳ እና የአውሮፓ ለአገሬዎቹ እና ለኢትዮጵያውያን አብያተ ክርስቲያናት ወንጌልን ሰብከዋል። ወደ እስካንዲኔቪያን እና ሌሎች የውጪ አገራትም ለአገልግሎት ተጉዘዋል።*

*የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የእምነት አቋም ሲቀረጽ፣ ስያሜና ዓርማዋ ሲወሰን፣ የመተዳደሪያ ደንብ ሲሻሻል በግንባር ቀደምትነት ሃሳብ ሰጥተዋል። በኮሚቴ አባልነት ሠርተዋል። አንዳንዴም በሰብሳቢነት መርተዋል። በመንገድ አብረዋቸው ለተጓዙም ሆነ በመኪናቸው ላሳፈሯቸው ወንጌልን ከመመስከር ጀምሮ እንደ የአዲስ አበባ ስታዲየም ባሉ ሰፋፊ የሕዝብ መሰብሰቢያዎች ወንጌል ሰብከዋል። ባሉበት አጥቢያ ከማስተማር ጀምረው በቃለ ሕይወትና በኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት የመሪዎች ኮንፍራንስ እንዲሁም በአገር ውስጥም ሆነ በውጪ በተካሄዱ ታላላቅ ጉባኤዎች ላይ አስተምረዋል።*

*በእነዚህ ሁሉ ዓመታትም የእግዚአብሔር መንፈስ እኚህን እራሳቸውን ፍጹም የሰጡ አገልጋይ በብዙ መልክ ተጠቅሞባቸዋል። ኬዳም በእነዚህ ሁሉ ዓመታት ካገለገሉባቸው ጸጋዎች መካከልም አምስት ዋና ዋናዎችን አንጥሮ ማውጣት ይቻላል። የወንጌል ሰባኪነት፣ የአስተማሪነት፣ የምክር ሰጪነት የማስታረቅ እና የጸሎት አገልግሎት።*

# 1.ወንጌል መስበክ

በ1944 ዓ.ም ጥቅምት ወር የቦቢቾ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ያላቸውን ጸጋ ለመለየት እንዲያግዝ ተብሎ በየማለዳው እንደሚደረገው አንድ ማለዳ ቃሉን ለተማሪዎች እና ለአስተማሪዎች እንድሰብክ እድል ተሰጠኝ። በዚያ ዘመን እኔ ገና ወጣት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ተማሪ ነበርኩ። በእርግጥ ከዚህ በፊት በአጥቢያው እንደ አንድ ጀማሪ አገልጋይ በማኅበራዊ እና በአነስተኛ የጸሎት ስብሰባዎች ላይ ቃሉን ሰብኬ አውቃለሁ። ነገር ግን በዚያ ጊዜ እግዚአብሔር በውስጤ ያስቀመጠው ታላቅ የስብከት ጸጋ እንዳለኝ ግን ገና እኔም በደንብ አላወቅሁም ነበር።

በዚያ የጥቅምት ማለዳ ለቦቢቾ ተማሪዎች እና መምህራን የሰባኪነት የጸጋ ስጦታ እንዳለኝ የሚያረጋግጥ መልእክት አቀረብኩ። በጊዜው በደንብ ጸልዬ ከዘፍጥረት ምዕራፍ 1-3 ድረስ ባለው የመጽሐፍ ቅዱስ ሃሳብ ዙሪያ በሚገባ ተዘጋጅቼ ስለሰው ታላቅ አፈጣጠር እና በኃጢአት አማካኝነት ስላጋጠመው ታላቅ አወዳደቅ ሰበኩ። በዚያች የመጀመሪያ የስብከት ዝግጅት ወቅት እግዚአብሔር በተጠቀሰው ክፍል ውስጥ ያለውን መልእክት እንደ ብርሃን ሲያበራልኝ፤ ከመልእክቱ የተነሳ መንፈስ ቅዱስ እንደ እሳት ውስጤን ሲያጥለቀልቀው ይሰማኝ ነበር። እናም በእለቱ ከተዘጋጀሁት በላይ በመንፈስ ሆኜ በእምባ የታጀበ የመጀመሪያ ድንቅ ስብከቴን አቀረብኩ። ያ እኔን የነካ መንፈስም በቦታው የነበሩትን መምህራን እና ተማሪዎች ሲያጥለቀልቅ አየሁ። በዚያች ዕለት እኔም ሆንኩ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቱ መሪዎች እግዚአብሔር እንዳገለግለው የሰጠኝን ጸጋ አየን። ወዲያው ለቀጣይ ከፍ ያሉ መንፈሳዊ ስብሰባዎች ሰባኪነትም አጩኝ። ከዚያች ዕለት አንስቶም በመላ ኢትዮጵያ ከዚያም አልፎ ወንጌልን በስፋት ከብዙ ሺዎች አልፎ ለሚሊዮኖች መስበክ የቻለ የወንጌል ሰባኪ ለመሆን በቃሁ።

ወንጌል የመስበክ ስጦታ እግዚአብሔር ራሱ የራሱን ሥራ ለመሥራት ስለፈለገ በኔ ውስጥ ያስቀመጠው ነው። እኔን ደግሞ ገና ከሰይጣን ባርነት አምልጬ በወንጌል ካመንኩበት ጊዜ ጀምሮ ኃያል የሆነ ወንጌልን የመስበክ ፍቅርን ሰጠኝ። እኔ እስከ ዛሬዋ እለት ድረስ ያገለገልኩበት እና ለእግዚአብሔር ራሴን ሰጥቼ የኖርኩበት ዋነኛ ምክንያት የክርስቶስ መስቀል ፍቅር ነው። የምኖረው የክርስቲያናዊ ኑሮ እና የማደርገው ነገር ሁሉ የመጀመሪያ ምክንያቱ እግዚአብሔር በልጁ በኩል ለኛ የገለጠው ፍቅር ነው። ደግሞም የምሰብከው ስብከት ሁሉ የመጀመሪያ ዋና መልእክት በክርስቶስ ሞት እና ትንሳኤ የተገለጠው ያ የመስቀል ፍቅር ነው። እግዚአብሔር ሲጠራው ለአገልግሎት የሚሠማራ የትኛውም አገልጋይ የመስቀሉ ፍቅር ባሪያ ነው።

እኔንም እግዚአብሔር ይህንን ታላቅ ፍቅር በልቤ ካቀጣጠለ በኋላ ሁል ጊዜ ስለዚህ ፍቅር እንዳውቅ፤ እንዳስብ፣ እንዳመሰግን፣ እንድጸልይ እንድኖር አደረገኝ። ስለዚህም ሁል ጊዜ ቃሉን እየከፈትኩ አነብባለሁ፤ ሁል ጊዜም እግዚአብሔር አዳዲስ

መልእክቶችን በልቤ ያፈስሳል። ከዚያም ወንጌሉን በተገኘው ቦታ እና በሁኔታዎች ውስጥ ሁሉ እሰብክ ነበር።

እግዚአብሔር ይህንን ክቡር የሆነ የወንጌል ሰባኪነት ሥራ ለእኔ የከብቶች እረኛ እና ገበሬ ለነበርኩት ሰው ሰጠኝ። እስከ ዛሬም በዚህ ምድር እስካለሁ ድረስ ሁልጊዜ ይህንኑ የወንጌል ሰባኪነት አገልግሎት እሰጣለሁ። በመንገድ ለሚሄድ አንድ ሰው፣ በእርሻ ቦታ አብሬ እየሠራሁ፣ በገበያ ቦታ፣ በለቅሶ እና የቀብር ስፍራ፣ በመኪና ስሄድ ተቸግረው አይቼ ለምጭናቸው ሰዎች፣ በልዩ ልዩ ስብሰባዎች፣ በመስጊድ እና በልዩ ልዩ ቤተ ክርስቲያናት ሳይቀር ስለ ክርስቶስ መስቀል ፍቅር ተናግሬአለሁ። እግዚአብሔርም ብዙ የሚያስደንቁ ድሎችን ሰጥቶኛል።

እግዚአብሔር ከሰጠኝ የስብከት የጸጋ ስጦታ የተነሳ እኔ በየትም ቦታ ሳስተምርም ቢሆን ከማስተምረው ትምህርት ወቅታዊ መልእክት የሚሆን ነገር አውጥቼ በአጭሩ እሰብካሁ። በልዩ ልዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች ለዘመናት ሳስተምርም በየእለቱ ከማዘጋጀው ትምህርት ውስጥ መልእክት አዘጋጅቼ ሳላስተላልፍ የትምህርቱን ክፍለ ጊዜ አልጨርስም ነበር። ይህ ልምምዴ በአስፈሪ ዘመን ለኔም ጭምር እምነትን የሚሰጥና ክፉ ዘመንን የሚያሻግር ሆኖኛል።

በደርግ ዘመን ቮልስ ዋገን መኪናዬን እየነዳሁ በጠዋት ወደ ጌጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ስሄድ ቫቲካን ኤምባሲ አካባቢ የማገኛቸውን ሰዎች እየጫንኩ እሄድ ነበር። መኪናዬ ውስጥ "በእግዚአብሔር ዘንድ ሁሉ ይቻላል" የሚል ጥቅስ ለጥፌ ስለነበረም ሁል ጊዜ ከዚያ ጥቅስ እየተነሳሁ ለምጭናቸው ሰዎች ወንጌል እሰብክ ነበር። ምንም እንኳን ዘመኑ እግዚአብሔር የለም የሚባልበት ቢሆንም ብዙ ሰዎች ደስ እያላቸው ይወርዱ ነበር። አንዳንዶች ጥቅሱን በእጃቸው እየደባበሱ "ለኔ ይሁንልኝ" እያሉ ሁሉ ይወርዳሉ።

አንድ ሰሞን የኢ.ሠ.ፓ ካድሬ የሆኑ ሁለት የሰፈሬ ሴቶች አብረውኝ ይሄዱ ስለነበር እኔም በድፍረት ወንጌልን እመስክርላቸው ጀመር። ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ሁለቱም አምነው ወደ እኔ ቤት እየተመላለሱ የደህንነት እና የጥምቀት ትምህርት አስተማርኳቸው። አንደኛዋ በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እያለች ስለተጠመቀች በድጋሚ መጠመቅ ባለመፈለጓ ከኔ ጋር ተነጋግረን ወደ መካነ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ሄዳ አባል ሆና እስከ ዛሬ ድረስ እዚያ እያገለገለች ጥሩ መንፈሳዊ ሕይወት ትኖራለች። ሌላዋ ተጠምቃ የኛ ቤተ ክርስቲያን አባል የነበረች ሲሆን ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ቤት ቀይራ ስለሄደች ተገናኝተን አናውቅም።

ጌታ በሰጠኝ በዚህ የወንጌል ሰባኪነት ስጦታ እና አደራ ሁል ጊዜ በደስታ እና በትጋት እያገለገልኩ ኖሬአለሁ። ምናልባት በሆነ አጋጣሚ ሳይሳካ ካልቀረ በስተቀር አንድም ቀን ወንጌልን ሰበክ ተብዬ ተጠይቄ ፈቃደኛ ሳልሆን ቀርቼ አላውቅም። እግዚአብሔርም አንድም ቀን በምሰብከው ስብከት የማስተላልፈውን መልእክት ሳይሰጠኝ ቀርቶ አያውቅም።

በሄድኩበትና በምቆምበት ሁሉ በኔ ተጠቅሞ እርሱ ሊያስተላልፍ የሚፈልገውን መልእክት አስተላልፏል። በአገሬ (ሻሾን) ሳስተምራቸው ከነበሩ ትንንሽ ሕፃናት ጀምሮ በአሜሪካ፣ በካናዳ እና በእንግሊዝ ባሉ ትላልቅ ቤተ ክርስቲያናት ያሉ ብዙ የተማሩ ዶክተሮች፣ ፕሮፌሰሮች፣ የተከበሩ ፈረንጆች እና ኢትዮጵያውያን መካከል በእኔ ያስተላለፈውን መልእክት ተጠቅሞ ሕይወታቸውን ሲነካ አይቻለሁ። ብዙ ከኔ የበላለጡ ታላላቅ ሰዎች የመጣላቸውን መልእክት በዕምባ ሲቀበሉና ንስኃ ሲገቡ፣ ጌታን ሲያመሰግኑና ጌታን ለመታዘዝ ሲወስኑ አይቻለሁ።

እኔ በራሴ ችሎታ አንድም ነገር ሳደርግ አልችልም ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር ይህንን ክቡር የጸጋ ስጦታ በኔ ውስጥ አስቀምጦ፤ የሸክላ ዕቃ በሆንኩት በኔ ውስጥ ድንጋይ የሚሰብር መልእክት አስተላልፎ፤ በድፍረት ሞልቶ፤ መገለጡን ሰጥቶ፤ ራእይ እና ዓላማውን አሳይቶ የብዙዎችን ሕይወት ለወጠ። ከግለሰብ ሕይወት አንስቶ በቤተሰብ፣ በማኅበረሰብ እና በአገር ደረጃ ብዙ ሥራ ሠርቶ አስደነቀኝ። ስሙ ለዘለዓለም የተባረከ ይሁን!!

# 2.ማስተማር

*ጊዜው አገሪቱ በወታደራዊ መንግስት የምትተዳደርበት ወታደራዊ መለዮ መልበስ እንደ አንደኛ ደረጃ ዜጋ የሚያስቆጥርበት ወቅት ነበር። ወንጌላዊ ኬዳሞ እንደተለመደው ለወንጌል አገልግሎት ዘመቻ በመላ አገሪቱ ይባትላሉ። በዚህ ወቅትም ባለቤታቸውን ጭምር ይዘው ወደ ወላይታ በመሄድ አገልግሎት ከሰጡ በኋላ ወደ አዲስ አበባ ለመመለስ አውቶብስ ተሳፈሩ። የተሳፈሩበት አውቶብስ ከአርባ ምንጭ ወደ አዲስ አበባ ሊሄድ ተነስቶ ወላይታ ያደረ ሲሆን ወንጌላዊው እና ባለቤታቸውም አውቶብሱ በነበረው ትርፍ ቦታ ላይ ነበር የተሳፈሩት።*

*አውቶብሱ የማለዳ ብርድ ያቆራመዳቸውን ተሳፋሪዎች አጭቆ ገና ሰማይና ምድሩ ሳይላቀቁ በሻሸመኔ በኩል አድርጎ ወደ አዲስ አበባ የሚያመራውን አስልቺ መንገድ ተያይዘው በአውቶብሱ የፊት ወንበሮች ላይ የተቀመጡት በአብዛኛው የልዩ ልዩ የጦር ሠራዊት ክፍሎች የጦር መኮንኖች ነበሩ። ጉዞው ተጀምሮ ጥቂት ሳይቆይም ወታደሮቹ እየተቀባበሉ የለኮሱት የሲጋራ ጭስ አውቶብሱን ሞላው። በዚህ ጊዜ የሲጋራ ጭሱ የረበሸው የተቀረው ተሳፋሪ ምንም ማድረግ አልተቻለውም። መስኮት ከፍተው ጭሱን እንዳያስወጡ በተከፈተው መስኮት የሚገባው ብርድ የባሰ አስቸጋሪ ነበር። ስለሆነም ሰው ሁሉ ከመኮንኖቹ አፍንጫ የሚትጎለጎለውን ለጤና ጠንቅ የሆነ የትንባሆ ጢስ እየታጠነ በፍርሃት መቀመጥ ግዴታው ሆነበት።*

*በዚህ ጊዜ ወንጌላዊ ኬዳሞ እና ባለቤታቸው አንድ ሙግት ገጠሙ። ወንጌላዊው ሄጄ መኮንኖቹን ሲጋራ መኪና ውስጥ እንዳያጨሱ ልንገር ሲሉ ባለቤታቸው ደግሞ "አይቻልም፤ ሄደህ ብትናገር ሌላ ችግር ታመጣለህ እንጂ አይሳካልህም" በሚል ሲከራከሩ ቆዩ። በመጨረሻም ኬዳሞ "እነዚህ አንድ ምድራዊ መንግስት የሾማቸው የጦር መኮንኖች ናቸው። እኔ ግን የሰማይ የምድሩ ፈጣሪ ሰዎችን ሁሉ እንዳስተምር የሾመኝ አገልጋዩ ነኝ። ስለዚህ ሄጄ እነዚህ ሰዎች እየሠሩት ያለው ጥፋት እንደሆነ አስተምራቸዋለሁ።" ብለው ተነሱ።*

*መኮንኖቹ ወደ ተቀመጡበት የአውቶብሱ ፊተኛ ወንበሮች በመሄድም ፊት ለፊታቸው ቆመው በጥበብ ቃል መናገር ጀመሩ። "እናንተ የዚህች አገር ጠባቂዎች ናችሁ። አንድ ሰው ይህቺን አገር ሊያጠፋ ቢፈልግ እናንተ ትከላከላላችሁ፤ ጥፋትን ታስቆማላችሁ፤ እናንተ ጥፋት ስትፈጽሙ ግን ማን ነው የሚያስቆማችሁ?" አሉ። እየተስገመገመ የሚወጣውን የወንጌላዊ ኬዳሞ የቁጣ ድምፅ መኮንኖቹ በጸጥታ ያዳምጡ ጀመር። "አሁን መስኮቱ በተዘጋጋ መኪና ውስጥ ሲጋራ እያጨሱ መሄድ ተገቢ ነው? ሌሎች ሰዎች ይህን ቢያደርጉ እናንተን ጠርተን አስቆሙልን እንላለን። እናንተ ይህን ስታደርጉ ግን እኛ ማንን እንጥራ?" መኮንኖቹ ወዲያውኑ በኀፍረት ስሜት እና በፍጥነት በእጅና በአፋቸው የያዙትን ሲጋራ እያጠፉ ወረወሩ። ወንጌላዊውንም*

*በአክብሮት ይቅርታ ጠየቁ። ኪዳኖም መኮንኖቹ አክብረው ስለታዘዟቸው አመስግነው አውቶብሱ ውስጥ የተሳፈረውንም ሰው የትንባሆ ጢስ ከመታጠን ታድገው ወደ ባለቤታቸው ተመለሱ።*

*አውቶብሱም ከሲጋራ ጢስ ብክለት ነጻ ሆኖ አዲስ አበባ ድረስ ገሰገሰ። በዚህ መልኩ ሲጓዙ ቆይተውም የጦር መኮንኖቹ ደብረ ዘይት ላይ መኪናውን አስቁመው ወረዱ። ወደ ኋላ የተቀመጡትንና ግብረገብ ያስተማሯቸውን ወንጌላዊ አመስግኖ መሰናበትን ግን አልረሱም።*

------------------------//------------------------

ማስተማር ማለት አንድን የተተከለ ተክል ውሃ ማጠጣት ወይም ደግሞ ሕፃን ልጅን እንዲያድግ ወተት ማጠጣት ማለት ነው። አንድን በወንጌል ያመነ ሰው እንዲያድግ ለማድረግ የግድ ማስተማር ያስፈልጋል። ማስተማር አንድ ሰው ሲያምን ማንን እንዳመነ፣ ለምን እንዳመነ፣ በእምነቱ እንዴት ማደግ እንደሚችል በደንብ እንዲያውቅ የማድረጊያ እና ያመኑትን ለአገልግሎት የማዘጋጃ መንገድ ነው።

እኔ በ1944 ዓ.ም ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ገብቼ መማር ከጀመርኩ በኋላ ለእረፍት ወደ ትውልድ ቀዬዬ ስመለስ በመጀመሪያ ያደረግሁት ነገር ያመኑትን ደጃፌ ላይ ሰብስቤ ማስተማር ነበር። ከዚያ ጊዜ አንስቶ እስከ ዛሬ ድረስም በየደረስኩበት ቦታ ሁሉ ወንጌልን ከመስበክ ጎን ለጎን ማስተማር ዋነኛ ሥራዬ ሆኗል።

እግዚአብሔር በወንጌል አምነው የዳኑ ሰዎች ሁሉ አድገው እንዲያገለግሉት ስለሚፈልግ ለኔ ልዩ የሆነ የማስተማር ፍቅርን ሰጠኝ። እኔም ሁል ጊዜ በማገለግልበት ስፍራ ሁሉ እቅድ አውጥቼ ቶሎ ማስተማር እጀምር ነበር።

ሻሾጎ ማስተማር ጀምሬ ሳገለግል ከቆየሁ በኋላ ወደ ጌዲኦ ስሄድም በነበረኝ ቆይታ ሁሉ ከሰኞ እስከ ዓርብ ዘወትር ጠዋት ጠዋት ከፊደል ማስቆጠር ጀምሮ ልዩ ልዩ መንፈሳዊ ትምህርቶችን ለዓመታት አስተምሬአለሁ። በዚህም እኛ የጌዴኦ ቤተ ክርስቲያንን ተሰናብተን ስንመለስ፤ ቤተ ክርስቲያኒቱን የሚረከቡ አገልጋዮችና መሪዎችን ማፍራት ችለን ነበር።

ሻሾጎ ተመልሼ አሸጎላም ሆነ ቢዲቃ እንዲማሩ እየሰበሰብኩ ፊደል ያስቆጠርኳቸው እና መሠረታዊ የክርስትና ትምህርቶችን ያስተማርኳቸው ሕፃናት እና ወጣቶች ዛሬ ገሚሶቹ ወንጌላውያን፣ ገሚሶቹ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አንዳንዶቹም በአዲስ አበባና በሌሎች ትልልቅ ከተሞች የሚኖሩ የተማሩ ሰዎች እና ነጋዴዎች ሆነው በያሉበት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በመሪነት እና በልዩ ልዩ የአገልግሎት ዘርፎች ውስጥ በማገልገል ላይ ይገኛሉ። ማረቆ እያለሁ ያመኑትን እና የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ማታ ማታ እስከ አምስት ሰዓት ድረስ በሳምንት ሁለት ቀን እያስተማርኩ ቤተ ክርስቲያንን እንዲረከቡ አዘጋጅ ነበር።

በቢቾ በነበርኩባቸው ሰባት ያህል ዓመታት በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ምክትል ዳይሬክተር እና አስተማሪ ከመሆን ባሻገር ወደ ሆሳዕና ከተማ እየተመላለስኩ በምሽት በሰባት ሰዎች ጀምሬ በኋላ ለ36 ሰዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት አስተምር ነበር። በየእሁድ ከሰዓቱ ደግሞ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ጳጳስ ሳይቀሩ በተገኙበት ልዩ ልዩ የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍትን በታላቅ ጉባዔ ፊት ሳስተምር ኖሬያለሁ። ከዚህ እግዚአብሔር ከከፈተው አስደናቂ የአገልግሎት በር የተነሳ ያኔ ሆሳዕና የማስተምርበት ቤት ለማግኘት እስክንቸገር ድረስ አንድም ጠንካራ አጥቢያ ያልነበረው ዛሬ በብዙ ትላልቅ አጥቢያዎች ተሞልታ እንደስሟ ሆሳዕና ሆና ሳይ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ።

ሆሳዕና በየሳምንቱ እሁድ ከሰዓት ሳስተምር በነበረበት ጊዜ ወንድሙ የሚባሉ ተመሳሳይ ስም ያላቸው ሁለት ልጆች እኔ ሳስተምር የተሳሳትኳቸውን የአማርኛ ቃላት ለቅመው በመያዝ ውጪ ወጥተው ያፌዙብኝ ነበር። አንድ ቀን እነዚህ ሁለት ልጆች መንገድ ላይ እየሄድኩ እያለ መጥተው እግሬ ላይ ወደቁ፤ ከዚያም "ሁል ጊዜ አንተ ስትሰብክ ከሰማን በኋላ ውጪ ወጥተን እንፎትት (እናሾፍ) ነበር። አሁን በቅርቡ እንደዛ ካደረግን በኋላ ግን ሁለታችንም ቤታችን ገብተን ባደረግነው ነገር ተጸጽተን ስንጨነቅ አድረናልና ይቅር በለን።" ብለው እየተንሯሯጡ መጥተው እግሬን ያዙና "ከዛሬ ጀምሮ በክርስቶስ እናምናለን።" አሉኝ።

ወደ አዲስ አበባ መጥቼ አገልግሎት ስጀምር ለጌጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን መሪዎች በመጀመሪያ ያቀረብኩት ጥያቄ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት እንዲከፈት ነበር። ያኔ ይህን ጥያቄ ሳቀርብ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ተማሪ አይገኝም በሚል ሃሣቤን ለመቀበል አመንትተው የነበረ ቢሆንም ትምህርት ቤቱ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ ለመቀበል ከምንችለው በላይ ተማሪ እየመጣ ብዙዎችን መልሰናል። በአንድ ዓመት ለምንቀበለው 40 ያህል ተማሪ ከ350 በላይ ትምህርት ፈላጊ ተመዝጋቢዎች ይመጡ ነበር።

ያኔ እኔ አስጀምሬው ለ20 ዓመታት በአስተማሪነት እና በርእሰ መምህርነት የሠራሁበት ትምህርት ቤት ይኸው ዛሬ አርባ ዓመት ሞልቶት እኔንም የክብር ዲግሪ ሸልሞኛል። ከሁሉ በላይ በተጀመረባቸው ዓመታት የነበረውን ስደት ተቋቁመን ከጌጃ ቃለ ሕይወት አልፎ ለመላው የኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት የተረፉ አገልጋዮችን አፍርተናል። በተለይ በደርግ ዘመን ልዩ ልዩ ቤተ ክርስቲያናት ተዘግተው በነበረበት ወቅት በሙሉ ወንጌል፣ በገነት፣ በአርነት እና በሌሎች በርካታ አብያተ ክርስቲያናት ዛሬ ትላልቅ ኃላፊነቶችን የያዙ አገልጋዮች ወደ እኛ መጥተው በመማር ለበለጠ አገልግሎት መዘጋጀታቸው በጣም ያስደስተኛል።

የማስተማር አገልግሎቴ በአጠቃላይ በሁለት ተከፍሎ ሊታይ ይችላል። አንደኛው በቤተ ክርስቲያንና በልዩ ልዩ ቦታዎች በርከት ያሉ ሰዎችን በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ክፍል ወይም በአጫጭር ርእሶች የማስተምርበት ሂደት ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ተተኪ አገልጋዮች እንዲሆኑ ጥቂት ሰዎችን ለብቻ ነጥዬ ይዤ የማስተምረው ነው።

ጌጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ሳለሁ አንዳንድ የላቀ እውቀት ያላቸው ሰዎች ሲያምኑ ለብቻቸው ነጥዬ አስተምራቸው ነበር። በአንድ ወቅት ዲያቆን አስጨናቂ የሚባልና በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ትልቅ እውቀት የነበረው ሰው አመነ። ይህ ወንድም ያለውን እውቀት በመረዳት ሁል ጊዜ ለብቻው ነበር የማስተምረው። በኋላም በሚገባ ተምሮ ከአገር እስከወጣበት ጊዜ ድረስ በቦሌ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ሆኖ ለረጅም ጊዜኗሯል።

ከዚህም ሌላ የወደፊት የቤተ ክርስቲያን ተረካቢ እንደሚሆኑና በውስጣቸው ጸጋ እንዳላቸው የማየውን እና ትልቅ አገልጋይ ይሆናሉ ብዬ የማስባቸውን እንዲሁ ለይቼ ለብቻ አስተምር ነበር። በጌጃ ቃለ ሕይወት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ስንጀምር እነ ሞገስ ታደሰን፣ ሽፈራው ፈይሳን፣ የኋላሸትን፣ ታደሰ ኢቢሳን፣ ሚካኤል ደንባውን ለብቻ ይገፔ በልዩ ትኩረት አስተምራቸው ነበር። እግዚአብሔር ይመስገን ዛሬ እነዚህ ሁሉ ትልልቅ የቤተ ክርስቲያን መጋቢያንና አገልጋዮች ሆነዋል።

የዛሬው መጋቢ ሽፈራው ፈይሳ ገና ታዳጊ እያለ ሰፈር ውስጥ እኔን ሲያገኝ ከኋላዬ እየተከተለ ይከምክና ያሾፍ ነበር። በኋላ ግን ያ ሲያሾፍበት የነበረው ቃል እርስትኑ መልሶ እንዳስለቀሰው አይቻለሁ። በትምህርት ብዙ ፍሬ ማፍራት እና የተጣመመውን ማቅናት ይቻላል።

በኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ዋና ጽሕፈት ቤት በኩል ማገልገል ከጀመርኩበት ጊዜ ጀምሮ እና ከዚያም ከለቀቅሁ በኋላ ማስተማር የአገልግሎቴ ዋና ክፍል ሆኖአል። በዋና ጽሕፈት ቤቱ በኩል በመላ አገሪቱ ያሉ የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያናት በቋሚ አገልጋይ እጦት ተጳከመው ቤተ ክርስቲያን በተበዘበዘችበት ጊዜ የጀመርነው አገልግሎት በትምህርት አገልጋዮችን የማፍራት እና የማዘጋጀት ሥራ ነበር። እኔና አጋሮቼ በመላ አገሪቱ በ80 ጣቢያዎች እየተዘዋወርንም ለ6 ዓመታት በተከታታይ በማስተማር ብዙ ሺዎችን ለፍሬ አብቅተናል።

ከ1995 ዓ.ም ጀምሮም ለ10 ዓመታት ያህል "የወንጌል ተልእኮ ዓላማና አፈጻጸም"፣ "ክርስቶስን መሰል ሕይወትና አገልግሎት" እና "የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች የወንጌል ባለ አደራዎች" በሚሉ ርእሶች ያዘጋጀኋቸውን ትምህርቶች በመጽሐፍ መልክ በማሳተም እያንዳንዱን ከ10 ሺህ ኮፒ በላይ አሰራጭቻለሁ። በዚህ የቅርብ ዘመን አገልግሎትም በርካታ አገልጋዮችን አስተምሬ ቤተ ክርስቲያን ብዙ ፍሬ አፍርታለች።

ማስተማር እግዚአብሔር የሰጠኝ ጸጋ ነው። ሆኖም እግዚአብሔር በኔ በኩል የሠራው ታላቅ ሥራ እኔ ሳስተምር ከምችለው በላይ የትምህርትን አስፈላጊነት በልቤ ውስጥ አብርቶ በደረስኩበት ሁሉ ትምህርት እንዲጀመር ምክንያት አደረገኝ። እኔ በከፍተኛ ደረጃ የተማርኩ ሰው አይደለሁም። ነገር ግን የእግዚአብሔር መንፈስ እያሳሰበኝ ትምህርት እንዲጀመር በተናገርኩባቸው ቦታዎች ሁሉ የተመሠረቱ የትምህርት ተቋማት ዛሬ ብዙ ሺህ ምሁራንን አፍርተዋል።

ሻሾን ውስጥ ምድር በኔ የተጀመሩት አራት ትምህርት ቤቶች ዛሬ እስከ 12ኛ ክፍል ድረስ ያስተምራሉ። በቅርቡ አርበጫ በሚባለው ቦታ ያስጀመርኩት ትምህርት ቤት 50ኛ ዓመቱን ሲያከብር እኔን አስታውሰው ትልቅ ጋቢ በስጦታ ልከውልኛል።

እኔ የጀመርኩት የጌጃ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት 40ኛ ዓመቱን ሲያከብርም የክብር ዲግሪ አበርክቶልኛል።

ይህም ብቻ ሳይሆን እኔ ክፍል ገብቼ ባላስተምርባቸውም የኤስ አይ ኤም መሪዎችን /በተለይም ያኔ ምን ሊደረግ ይገባል ብለው በመላ ቃለ ሕይወት ለዞሩት ሚ/ር ሃዊ ለቃለ ሕይወት ሊያደርጉት ይገባል ብዬ የወተወትኳቸው አራት የመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጆችን የመክፈት ሃሳቤ እውን ሆኖ የዲላ፣ የሶዶ፣ የዱራሜ እና የቦቢቾ መጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጆች ለኔ ትልቅ የደስታ ምንጭ ሆነውኛል።

የዲላ አገልጋዮች ማሰልጠኛ ኮሌጅ በተከፈተበት ወቅት በተካሄደው ምረቃ ላይ የክብር እንግዳ ሆኜ ተገኝቼ የምስጋና ጸሎት እንድመራ የተጋበዝኩት እኔው ነበርኩ። ከእነዚህ ሁሉ በላይም ገና በጌጃ የአንድ አጥቢያ አገልጋይ እያለሁ የጌጃ ቃለ ሕይወት ሽማግሌዎችን በማሳመን በዋና ጽሕፈት ቤት ደረጃ በዲግሪ የሚያስመርቅ ኮሌጅ እንዲከፈት ጥያቄ አቅርበን ነበር። ሆኖም በወቅቱ ዋና ጽሕፈት ቤቱን ይመሩ የነበሩ ኃላፊዎች ነገሩን ለማስፈጸም ስላልቻሉ ጥያቄውን ለኛው መልሰውት እኔ ተመላልሼ የኤስ አይ ኤም ሚስዮናውያንን ለማሳመን ጣርኩ። በወቅቱ የኤስ አይ ኤም ኃላፊ የነበሩት ፖል ቢልስኪን የሚኖሩበት ዘነበወርቅ ድረስ ሄጄ ጥያቄውን አቅርቤላቸው አብረን ጸልየናል። ከእርሳቸው በኋላም ተወዳጁ ሚስዮናዊ እና አስተማሪ ሚ/ር ስቲቭ ስትራውስን እና በአይ.ኢ.ሲ ቤተ ክርስቲያን የወቅቱ መጋቢ ለነበሩት ሰው በተደጋጋሚ ይህን ጥያቄ አቀርብላቸው ነበር።

ያኔ አራት በዲፕሎማ እና አንድ በዲግሪ ደረጃ የሚያስተምሩ ኮሌጆች ያስፈልጋሉ ስል በኮሚኒስት መንግስት ዘመን እንዴት ይሆናል ሲሉ የነበሩ የኤስ አይ ኤም ሚሲዮናውያን ሃሳባቸውን ለውጠው በስተመጨረሻ እንደ አራቱ ኮሌጆች ሁሉ በዲግሪ የሚያስተምረው ትምህርት ተቋም በመጀመሪያ ምንም ሥርተፍኬት አይሰጥ ዝም ብሎ ትምህርቱን ያካሂድ በሚል ሃሣብ ተስማምተን በኔ ጥያቄ መሠረት በኤስ.አይ.ኤም እንዲሆን ተወስኖ ትምህርቱ ተጀመረ። እግዚአብሔር ይመስገን ዛሬ ለመላ የአገራችን አብያተ ክርስቲያናት በረከት የሆኑት ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሩቃን ከዚያም በዶክትሬት ደረጃ የተማሩ ምሁራንን ለማፍራት ችለናል። እግዚአብሔር ይመስገን።

ማስተማር ለቤተ ክርስቲያን የጀርባ አጥንት የሆነ የአገልግሎት ጸጋ ስለሆነ ብዙ ፍሬ ማፍራት ያስችላል። በማስተማር አገልግሎት ብዙ ምስክርነቶች የነበሩ ቢሆንም በታሪክ ውስጥ በስፋት ስለተጠቀሰ በዚሁ ላብቃ እና ወደ ቀጣይ የአገልግሎት ስጦታዬ ልለፍ።

# 3.ምክር

መጽሐፍ ቅዱስ "የሚመክር በመምከሩ ይትጋ" ይላል (ሮሜ 12፡8) ። ምክር አገልጋዮች ሁሉ ሊኖራቸው የሚገባ የአገልግሎት ጸጋ ነው። ጌታ ኢየሱስ በኢሳይያስ መጽሐፍ ከተሰጡት ስሞች አንዱ "ድንቅ መካር" የሚል ነበር። ይህ መልካም መካሪ የሆነ ጌታ እኔንም ለአገልግሎቱ ዓላማ እንዳውለው የምክር ጸጋን ሰጥቶኝ ለብዙዎች ሕይወት መለወጥ ምክንያት አድርጎኛል። መምከር የወደቀን ማንሳትና ተስፋ ቆርጦ ግራ የገባውን ከተስፋ ጋር ማገናኘት ነው።

በቢቾ እያገለገልኩ በነበረበት ጊዜ ኮንቶም በሚባል ከ50 በላይ አጥቢያዎች ባሉት የአካባቢው ክፍለ ማኅበር የስሕተት ትምህርት ገብቶ ነበር። በወደዚህ ክፍለ ማኅበር የገባው የሐሰት ትምህርት ልክ በሐዋርያቱ ዘመን እንደሆነው "ምንም አይነት የራስ ንብረት ማፍራት እንደማይገባ እና ያለንን ሁሉ ለቤተ ክርስቲያን መስጠት አለብን" የሚል ሲሆን ከዚህም ሌላ "ክርስቲያን ፈጽሞ ኃጢአት ሊነካው አይገባም፤ እውነተኛ ክርስቲያንም ጨርሶ ኃጢአት አይሠራም" ብለው ያስተምሩ እና ያምኑ ነበር።

ከዚህ የተነሳም ብዙ አጥቢያዎች እና አገልጋዮች ትምህርቱ ልክ ነው ብለው ከዋናው የከምባታና ሃዲያ ኅብረት ተነጥለው ቀሩ። ቢጊራ በሚባል ቦታ የኅብረቱ ጉባኤ ሲካሄድም የተገነጠሉት በሙሉ ቀሩ። ጉባዔው በተካሄደበት ወቅት ለምን እንደቀሩም ባለመታወቁ እኔ ከዚያ ክፍለ ማኅበር የመጡ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎችን ስጠይቅ ስለተፈጠረው ነገር እና ስለ ተጀመረው የስህተት ትምህርት ነገሩኝ።

ከዚያም አንድ ረቡዕ እለት ተነስቼ ወደዚያው ሄድኩ። በሄድኩበት ዕለት ጠዋት ከ3፡30 ጀምሮም የዚህ ትምህርት ተከታይ የቤተ ክርስቲያን አባላት ቤተ ክርስቲያን ሞልተው ባሉበት ከዚህ ትምህርት ዋነኛ አስተማሪ ጋር እስከ ሌሊቱ 9፡00 ሰዓት ድረስ ውይይት አደረግን። በሕዝቡ ፊት ስለ እያንዳንዱ ጉዳይ እያነሳሁም እየጠየቅሁት በቀስታ ብዙ ስመክረውም ቆየሁ። ብዙ ከጠየቅሁት በኋላም ለእያንዳንዱ መልስ እያጣ ሲቸገር ሕዝቡ ያይ ነበር። በመጨረሻም "አንድ ሰው ምንም ኃጢአት ሊነካው አይገባም ብለሃል። ታዲያ ጌታ ኢየሱስ ጸሎት ሲያስተምር ለምን "... በደላችንን ይቅር ብለን ብላችሁ ጸልዩ" አለ" አልኩት። የሚመልሰው አጥቶ ዝም አለ። "እናስ አሁን አልተሳሳትክምን?" አልኩት። አሁንም ዝም አለ።

ሕዝቡም ይህን አየ እና አሁን አንድ ነገር ገብቶናል፤ እኛ ብቻ ሳንሆን ክፍለ ማኅበሩ በሙሉ ይሰብሰብ፤ እናንተም ኑ ብለው ቀጠሮ ሰጥተውኝ ተመለስኩ። በኋላም አቶ ዳምጤ ከሚባሉ ሌላ አገልጋይ ጋር ሆነን ሄድን።

በመጀመሪያ በስፍራው ስንደርስ የኛ ወዳጆች የነበሩ ሰዎች ተቆጥተው "ሕዝቡ እና እኛ ለጌታ ከተሰጠንበት ሕይወት ልትመልሱን ነው። ወደ ተሰበሰበው ጉባዔ አትግቡ"

አሉን። በውጪ ብዙ ምክክር ካደረግን በኋላም እንድንገባ ተፈቅዶልን አራታችንን በልተን ምንም ሳንነጋገር አደርን።

በማግስቱ በማለዳ ሕዝቡ ሁሉ ባለበት እኔን መልእክት እንዳቀርብ ጠየቁኝ። እኔም "ህያው መስዋዕት" በሚል ርዕስ በሮሜ.12 ላይ ያለውን ሃሳብ አካፈልኳቸው እና በሐዋርያት ዘመን እንዴት ገንዘባቸውን እንደከፈሉ ንብረታቸውንም ለጌታ እንደሰጡ ካብራራሁ በኋላ ወደ ውይይት ገባን። እኔም እኛም ሆንን የእኛ የሆነው ሁሉ የእግዚአብሔር እንደሆነ በዚህ ዘመን ግን ኃብታችንን እንዴት ማድረግ እንዳለብን በመጠየቅ በሐዋርያት ዘመን እንኳን ነገሮች በዚያው መልክ እንዳልቀጠሉ አስታወስኳቸው። "እኛም ክብት እያረባን እርሻ እያረስን ከምናገኘው አስራት ብንሰጥ ይሻላል? ወይንስ አንድ ጊዜ ሁሉን ሰጥተን ምንም ባይኖረን ይሻለናል?" የሚል ጥያቄ አቅርቤላቸው ተወያየን። በመጨረሻም ሕዝቡ ሁሉ ተስማምቶ ከስሁተት ትምህርት ተመለሱ። ይህ ጌታ የሰጠኝ የምክር አገልግሎት ውጤት ይመስለኛል።

ጌጃ ቃለ ሕይወት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በነበርኩበት ጊዜም ሰባት ጊዜ የስህተት ትምህርቶች ተነስተው ከማያስተምሩ ሽዎች ጋር ቁጭ ብለን በመነጋገርና በመመካከር ከሳቱበት እየተመለሱ ማንም እምቢ ብሎ ሳይወጣና ሳይኮበልል መቀጠል ችለናል። ምክር ሰው እንዳይኮበልል እና ከጌታ ክብርም እንዳይጎድል ያደርጋል።

በምክር አገልግሎቴ የቤተ ክርስቲያን አባላትን እየዞርኩ በመጎብኘት በትዳራቸው፣ በኑሮአቸው፣ በቤተሰባዊ ግንኙነታቸው ዙሪያም እንደግፋቸው ነበር። ጌጃ ቃለ ሕይወት አንድ የቤተ ክርስቲያናችን አባል በፔፕሲ የለስለሳ መጠጥ ፋብሪካ ውስጥ ተቀጥሮ እየሠራ ሁል ጊዜ 5 ብር በወር አስራት እያመጣ በታማኝነት ይከፍል ነበር። እኔ ልጎበኛቸው ወደ ቤታቸው ስሄድ ይህ አባላችን ከባለቤቱ ጋር ልጅ ወልደው በከፋ ችግር ውስጥ እንደሚኖሩ አየሁ። ከዚያም የሚያገኘው በወር 50 ብር ደመወዝ በቀን ስንት ብር ሊሆን እንደሚችል ቁጭ ብለን ስናሰላ 1 ብር ከ50 ሳንቲም ገደማ መጣ። እና እኔም "በቀን 1.50 ለማግኘት ብለህ ከምትለፋ የቀን ሥራ ብትቀጠር በቀን 7ብር የሚከፍልህ ታጣለህ ወይ?" ስለው "አላጣም" አለኝ። "ታዲያ እግዚአብሔር የሰጠህ ጉልበት ለምን በከንቱ ይበዘበዛል? በቃ ያንተ ጉልበት የእግዚአብሔር በመሆኑ ሠርተህ ተገቢውን ማግኘት አለብህ።" ብዬ እግዚአብሔር በረዳኝ መጠን የተስማኝን መከርኩት። በምክሩ ልክ ወይን ጠጅ እንደጠጣ ሰው ሰከረ። ሁለተኛ ተመልሶ ወደ ቀድሞ የሥራ ቦታው አልሄደም።

ወዲያው አንድ የውሃ ሥራ ከሚሠራ ሰው ጋር በቀን ሠራተኛነት ለመቀጠር ጠይቆ በቀን ዘጠኝ ብር እየተከፈለው ለመሥራት ተስማምቶ ተቀጠረ። ለሦስት ወራት ብቻ ያንን ሥራ ሠርቶ ልምድ ካገኘ በኋላም ወለጋ የውሃ ቱቦ መስመር ዝርጋታ ሥራ ኮንትራት ወስዶ በሁለት ወራት ሥራ ብቻ 3,000 ሦስት ሺህ ብር አግኝቶ መጣ። ዛሬ በመላ ኢትዮጵያ እየተንቀሳቀሰ የውሃ ቧንቧ ዝርጋታ ሥራ የሚሠራ የታወቀ ባለሙያ ሆኗል። ከብዙ ዓመታት በኋላ ሐዋሳ ከተማ ውስጥ ከባለቤቱ ጋር ትልቅ ሆቴል አልጋ ይዘው እየተዝናኑ አገኘኋቸው።

ከዚህም ሌላ በጌጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን አገልግሎቴ ወቅት በዓመት ሁለት ጊዜ በጉባኤ ደረጃ ስለሥራ አስተምር ነበር። ይህንንም መልዕክት የሰጠኝ መንፈስ ቅዱስ ነው። የሰው ልጅ ሰውነት ምን ያህል ክቡር እና ውድ እንደሆነና አንድ ዓይን እንኳን በሚሊዮኖች ብር ልትገኝ እንደማትችል በመግለጽ ይህንን ሁሉ አካል እግዚአብሔር እንድንሠራበት እንደሰጠን እናገራለሁ። ደግሞም ጌታ ኢየሱስ "አባቴ እስከ ዛሬ ይሠራል፤ እኔም ደግሞ እሠራለሁ።" እንዳለው ሁሉ ሁላችን ልንሠራ እንደሚገባን አስተምራለሁ። ክርስቲያኖች ሁሉ በትጋት መሥራት እንዳለብን፣ ሳይሠራ የተቸገረን መርዳት እንደማይገባና ይልቁንም ክርስቲያኖች ሠርተው ሌሎችን መርዳት እንዳለባቸው በመናገር አባላትን ለሥራ አነሳሳ ነበር። ከዚህ የተነሳም በጌጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ሰዎችን ለሥራ ለማነሳሳት የሙያ ትምህርት ተጀምሮ ብዙ ወጣቶች ተጠቃሚ ሆነዋል።

ይህን በሥራ ትጋት ዙሪያ የምሰጠውን ምክር የጀመርኩት ከብዙ ዓመታት በፊት ነበር። በ1955 ዓ.ም ከማረቆ ተመልሼ የእርሻ ሥራ በምሠራበት ወቅት ትጉህ ገበሬ ስለነበርኩ በአንድ ጊዜ ብዙ ሃብት እንዳገኘሁ ቀደም ሲል ተርኬላችኋለሁ። በዚሁ ጊዜ አንድ የክፍለ ማኅበራችን መሪ የነበረ የአጎቴ ልጅ የተከበረ የቤተ ክርስቲያን መሪ ሆኖ እርሻውን እያረሱለት ለእኩል የሚካፈሉ ገበሬዎች ነበሩ። እኔም እርሱ እርሻ ማረስ ተጠይፎ ከገበያ ቆጮ ሲገዛ ሲሄድ ስላየሁት፤ "አንተ እርሻ አላርስም ብለህ ከገበያ ቆጮ ልትገዛ ትሄዳለህ፤ አንተ የተከበርክ የቤተ ክርስቲያን መሪ ሆነህ ይህን ስታደርግ የትኛው ነው ላንተ ክብር የሚሆነው? እርሻ ማረስ ወይስ ቆጮ ከገበያ መሸመት?" አልኩት። በዚህ ጊዜ ደንግጦ ከእንቅልፉ እንደሚነቃ ሰው ነቅቶ ወደ ማስተዋል መጣና ወዲያውኑ እርሻውን ለእኩል ማሳረሱን አቁሞ ራሱ ማረስ ጀመረ።

አንድ ቀን እኔን ሲያገኘኝም "ኬዳሞ መሬቴ ጠበበኝ" አለኝ። እኔም "አዎ ድሮ ያንተ አእምሮ ጠባብ ስለነበረ መሬትህ ሰፊ ሆነብህ፤ አሁን ግን ያንተ አእምሮ ስለሰፋ መሬቱ ጠብቦሃል" አልኩት። ይህ ዘመዴ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ በትጋት ስለሠራ ለረጅም ጊዜ የተባረከ ኑሮ እየመራ እግሩ መሬት ሳይነካ በበቅሎ እየሄደ በቅርቡ ወደ ጌታ እስከሄደበት ጊዜ ድረስ በምቾት ኖረ።

ልክ እንደዚሁ እርሻውን ለሚስቱ ወንድሞች ሰጥቶ እርሱ ጋቢ ለብሶ ሲዞር የሚውል ሌላ የአጎቴን ልጅ "ሚስትህ አንድ ቀን ብትቸገሩ 'አይ እርሻውን ለወንድሞቼ ሰጥቷል' ብላ ዝም ትልሃለች ወይ?" አልኩት "አትለኝም" አለ። "ታዲያ አንተ ጤነኛ ነህ፤ ለምንድነው እርሻህን ራስህ የማታርሰው?" አልኩት። ወዲያው መሬቱን ከአማቾቹ ወስዶ እራሱ ማረስ ጀመረ። ዛሬ ሀብታም ሆኖ ልጆቹን እስከ ዩኒቨርስቲ ድረስ ማስተማር ችሏል።

በ2001 ዓ.ም ወደ ሻሾጎ ሄጄ 500 ለሚያህሉ ወጣቶች ሥልጠና ሰጥቼ ነበር። በሥልጠናው መጨረሻ ላይ ስለሥራ ምክር ሰጠኋቸው። አስቀድሜም የኢትዮጵያ ድህነት መንስኤን ስጠይቃቸው ብዙ ነገሮችን ጠቃቀሱ። እኔም "ሌሎቹ ተጨማሪ ቢሆኑም ዋናው ግን ስንፍና ነው" ብዬ ሰነፍ መሆን እንደሌለባቸውና በትጋት

መሥራት እንደሚገባቸው አስተማርኳቸው። ደግሞም በሻሾን ምድር 8 ሜትር ጥልቀት ቢቆፈር ውሃ ሊገኝ እንደሚቻል እና ያንን በመጠቀም በጋና ክረምት የተለያዩ አትክልቶችን እና በርበሬ ማምረት እንደሚቻል መከርኳቸው።

በቅርቡም ሻሾን ያሉ የኛ ጎሳ አባላት በአገር ጉዳይ ሊመክሩ ተሰብስበው እኔንም ጠርተውኝ ነበር። በዚሁ ጊዜ ዋናው የመወያያ አጀንዳ የነበረው "ወጣቶች በስደት ወደ ደቡብ አፍሪካ እንሄዳለን ብለው ከአገር እየወጡ በአደጋ እያለቁ ነው" የሚል ነበር። እናም ምን ማድረግ አለብን ለሚለው ጥያቄ የጎሳ ዳኛ የሆኑ ግለሰብ ተነስተው "በኛ አካባቢ መንግስት ፋብሪካ ተክሎ ወጣቱ ሥራ ካላገኘ ዋጋ የለውም" አሉ። እኔ ግን ያኔ ወጣቶቹን ያስተማርኩትን በሻሾን ያሉ ወጣቶች በቀላሉ ጉድጓድ ቆፍረው ውሃ በማውጣት አትክልት አምርተው በመሸጥ ሕይወታቸውን መቀየር እንደሚችሉ ስናገር ሁሉም ሰው በኔ ሃሳብ ተስማማ። ከዚህ ምክር የተነሳ ዛሬ ብዙ ወጣቶች እየደወሉልኝ "በርበሬ ተክዬ 8 ሺህ ብር አገኘሁ፤ 11 ሺህ ብር አገኘሁ ወዘተ ..." ይሉኛል።

የምክር አገልግሎት ለቤተ ክርስቲያንም ሕልውና መሠረት የሆነ አገልግሎት ስለሆነ አገልጋዮች የሚያገለግሉትን ሕዝብ ሁል ጊዜ ሊመክሩ ይገባቸዋል። ብዙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እና አገልጋዮች ምክር በማጣታቸው ቤተ ክርስቲያን ችግር ውስጥ ትወድቃለች።

በቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ዋና ጽሕፈት ቤት ለቤተ ክርስቲያኒቱ ትንሳኤ እናመጣለን ብለን ስናካሂድ በነበረው የብሔራዊ ወንጌላውያን አገልግሎት ሂደት ከዋናው የማስተማር አገልግሎታችን ባልተናነሰ ታላቅ ለውጥ ያመጣው የምክር አገልግሎት ነበር። ይህ ትልቅ ለውጥ እንዲመጣ የረዳው የምክር አገልግሎትም እንዲህ ነበር የሚካሄደው።

ሁል ጊዜ በየትም ቦታ ሥልጠና እና ኮንፍራንስ ከተካሄደ በኋላ ያንን ሥልጠናና ኮንፍራንስ ካዘጋጁ የቤተ ክርስቲያን፣ የክፍለ ማኅበር ወይም የኅብረት ጽሕፈት ቤት መሪዎች ጋር እግዚአብሔርን ለማመስገን እና ለመባረክ እንሰባሰባለን። በዚህ ጊዜ እኛ ለዚያ ቤተ ክርስቲያን ወይም የኅብረት ማስተባበሪያ ጽሕፈት ቤት ሰባት መሠረታዊ ጥያቄዎችን እናቀርባለን። ጥያቄዎቹም፡-

1. በአጥቢያችሁ ወይም በምታስተባብሩት ኅብረት ውስጥ ምን ያህል ምዕመናን አሉ?
2. በመሪነት የሚያገለግሉ ምን ያህል ሽማግሌዎች አሉ?
3. በመደበኛነት የሚያገለግሉ ምን ያህል የሙሉ ጊዜ (ወንጌላውያን/መጋቢያን) አሉ?
4. አጠቃላይ አገልግሎቶችን ለማካሄድ የተዘጋጀው እቅድ እና ፕሮግራም ማስፈጸሚያ መርሃ ግብር ምን ዓይነት ነው?
5. የቤተ ክርስቲያኒቱ ወይም የጽሕፈት ቤቱ የገቢ ምንጭ ምንድን ነው?

6. የቤተ ክርስቲያኒቱ ወይም የጽሕፈት ቤቱ የገንዘብ አያያዝ ሁኔታ ምን ይመስላል?
7. በቤተ ክርስቲያኒቱ ያለ ወቅታዊ ችግር ምንድነው?

የሚሉ ሲሆኑ የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪዎችም ለጥያቄዎቹ በደንብ እየተወያዩ ምላሽ ይሰጣሉ። ከዚህ በመነሳትም እኛ በቤተ ክርስቲያኒቱ ወይም በጽሕፈት ቤቱ ችግር ያለበትን አቅጣጫ ለይተን በማወቅ ተገቢውን ምክር እንሰጣለን። በዚህ መልኩም የቤተ ክርስቲያኒቱ ወይም የጽሕፈት ቤቱ ችግር ይፈታል።

አንድ ጊዜ እኔ እና የብሄራዊ ወንጌላውያን ቢሮ ባልደረባዬ አዱኛ ለሥልጠና ወደ አለታ ወንዶ ሄደን ነበር። በዚሁ ጊዜም በዚያ ኅብረት ጽሕፈት ቤት ሥር ላሉ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በጠቅላላ ሥልጠና ስንሰጥ ቆየን። ከሥልጠናው ቀናት በአንዱም እኔ ሥልጠና ስሰጥ ቆይቼ ተራውን ለአዱኛ አስረክቤ እና እርሱ እያሰለጠነ እያለ እረፍት ለማድረግ ወደ ውጪ ወጣሁ። አለታ ወንዶ በሥሩ ከ100 በላይ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናትን የሚያስተባብር የኅብረት ጽሕፈት ቤት ሲሆን የአለታ ወንዶ ከተማ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንም በዚሁ ግቢ ትገኛለች። እኔ በዚሁ ግቢ እየተንሸራሸርኩ እያለም ያ ግቢ ያኔ በንጉሡ ዘመን ለሚሲዮናውያን ተሰጥቶ በኋላም ለቤተ ክርስቲያናችን የተሸጋገረ ሲሆን በጣም ሰፊ ባዶ መሬት ለዓመታት ያለ ምንም አገልግሎት ተቀምጧል። በዚህ ጊዜ እኔ በውስጤ አንድ ሃሳብ ተፈጠረ። ወዲያውም ቀጣይ የማስተማሪያ ጊዜዬ ስለተቃረበ ሥልጠናው እየተካሄደበት ወደነበረው የቤተ ክርስቲያኒቱ አዳራሽ አመራሁ።

እኔ የማስተምርበት ክፍለ ጊዜ ሲደርስም የነበሩትን ሠልጣኞች በሙሉ ከክፍል አስወጥቼ ወደ ሜዳው ሄድን። ከዚያም በግቢው ያለውን ለእርሻ ምቹ የሆነ ሰፊ ቦታ በማሳየት ቡና ቢተከልበት ለቤተ ክርስቲያኒቱ ከፍተኛ ገቢ ሊያስገኝ እንደሚችል በመንገር እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን የሰጠውን ሃብት እንደሚገባ መጠቀም እንደሚገባቸውም አስተማርኳቸው።

በዚህ መልኩ ሥልጠናው ተጠናቅቆ ኮንፍራንስ ተካሄደና የእኔና የአቶ አዱኛ የመመለሻ ቀን ሲደርስ እንደተለመደው መሪዎችን ሰብስበን ሰባቱን ጥያቄዎች አቀረብንላቸው። በወቅቱ የኅብረቱ ጽሕፈት ቤት ምንም ገቢ እንደሌለው በውስጡ ለሚያገለግሉት ወንጌላውያንም ደመወዝ መክፈል እንዳልተቻለ እና እስከአሁን ያወጡት 71 ሺህ ብር ዕዳ እንዳለባቸው ነገሩን።

እኛ በሄድንበት በመጋቢት ወር ለአገልጋዮቹ ለሁለት ዓመት ያህል ደመወዝ እንዳልተከፈላቸው የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪዎችም በዕዳ ብዛት እየተጨናነቁና ድጋፍ ፍለጋ እዚህ እና እዚያ እያሉ እየለመኑ በጣም እንደተቸገሩ ነገሩን። በዚያ ወቅትም በእጃቸው በግቢው ያለው ሣር ተሸጦ ከተገኘ 1000 ብር በስተቀር ምንም እንደሌላቸው ነገሩን። ይህንን ስንሰማ እኛም በጣም በማዘን ሁላችንም ተንበርክከን እያለቀስን በጉዳዩ ላይ ጸለይን። ከዚያም ቁጭ ብለን ምክክር አደረግን፤ በኋላም ከፊታችን በነበረው

የግንቦት ወር በኅብረቱ ውስጥ ያሉ አጥቢያዎች አጠቃላይ መሪዎች ማለትም የወጣት እና የሴቶች አገልግሎቶች መሪዎችን ጨምሮ በአጠቃላይ 21 የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከእያንዳንዱ አጥቢያ መጥተው በጨኮ ከተማ ኮንፍራንስ ለማድረግ በመስማማት እኛ በማግስቱ ወደ አዲስ አበባ ተመለስን።

የተቀጠረው የግንቦት ወር ሲደርስም እኔ እና ዶ/ር ደስታ ላንገና ሆነን ወደ ጨኮ ሄደን አገለገልን። በወቅቱ ከየአጥቢያው የተጠሩ መሪዎች በሙሉ በታማኝነት መጥተው 1800 ያህል ሰዎች ተገኝተው ነበር። እኛም ትምህርት ካስተማርን በኋላ አጠቃላይ ጉባኤው ባለበት በዚያ ኅብረት ግቢ እና በወንጌል አገልግሎት እድገት ዙሪያ በእኔ ሰብሳቢነት ሰፊ ውይይት ተካሄደ። በውይይቱ ጅማሬ ላይም የተገኙት መሪዎች በኅብረቱ ወቅታዊ ሁኔታ ልባቸው ተነክቶ ስለነበር በተሰበረ ልብ በጌታ ፊት ቀረቡ። ብዙዎችም በጌታ ፊት እያለቀሱ ንስሃ ገቡ።

ውይይቱን ካደረግን በኋላም እዚያው ከተሰበሰበው ጉባኤ ገንዘብ ተሰብስቦ በእለቱ 90 ሺህ ብር ተገኘ። ቤተ ክርስቲያኒቱ የነበረባት 70 ሺህ ብር እዳ ተከፍሎም ለቀጣይ ሥራ 20 ሺህ ብር ትርፍ ተገኘ። መሪዎችም በተመካከርነው መሠረት ተጨማሪ የገቢ ማግኛ ስልቶችን ቀየሱ። ከዓመታት በኋላ አስቀድሜ በመከርኳቸው መሠረት የተከሉት ቡና ደርሶም ጥሩ ተጨማሪ ገቢ እንዲያገኙ ረዳቸው። ዛሬ ያ ኅብረት በብዙ እጥፍ ተባርኮ በልዩ ልዩ አቅጣጫዎች ለወንጌል ሥራ የሚዘረጋና ከራሱ አልፎ ለሌሎች ድጋፍ የሚያደርግ ሆኗል።

ይህን የምክር አገልግሎት በአለታ ወንዶ ብቻ ሳይሆን የከፋ ችግር ላይ ለነበረችው የይርጋ ጨፌ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ኅብረት ጽሕፈት ቤትም ተጠቅሜበታለሁ። ለወንጌል ስርጭት ስልጠና ሄጀ በነበረበት ወቅት በሥልጠናው ማብቂያ ላይ አካሂጀው ለቤተ ክርስቲያኒቱ ትልቅ ፈውስ ያመጣ ሥራ መሠራቱን አስታውሳለሁ። ያኔ በይርጋ ጨፌ ልክ በአለታ ወንዶ እንደተደረገው አይነት ጥያቄ ባቀረብኩበት ጊዜ አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ በወቅቱ ያቺ ቤተ ክርስቲያን (የይርጋ ጨፌ ኅብረት) የነበረችበትን አሳዛኝ ሁኔታ ነገረኝ። በወቅቱ ቤተ ክርስቲያኒቱን ቀደም ሲል ሲመሩ የነበሩ መሪዎች ገንዘቡን ለግል ጥቅማቸው በማዋላቸው ምክንያት በኅብረቱ ውስጥ መተማመን ጠፍቶ አንድም ለኅብረቱ ሥራ ማስኬጃ የሚሰጥ አጥቢያ ቤተ ክርስቲን አልነበረም። ከዚያም በችግሮቹ ዙሪያ በአጠቃላይ በኅብረቱ ውስጥ ያሉ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንዲገኙ ካደረግን በኋላ ለመሪዎች በሰጠሁት ትምህርት እና ምክር ቤተ ክርስቲያኒቱ ከችግር ወጥታ አሁን በቃለ ሕይወት ካሉ ጠንካራ ኅብረቶች መካከል አንዷ መሆን እንደቻለች አይቻለሁ። በዚህ ሁሉም በኔ የምክር አገልግሎት ተጠቅሞ ለቤተ ክርስቲያን ፈውስ እና በረከት ያመጣውን ጌታ እባርካለሁ።

# 4.እርቅ

በማስታረቅ አገልግሎት ውስጥ ክርስቲያኖች ሁሉ መሳተፍ እንዳለብን በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈ ነው። ሆኖም የማስታረቅ አገልግሎት የሚሰጥ አስታራቂ የሚኖረው ማስተዋል እና ጥበብ እንዳለ ሆኖ በታራቂዎቹ ዘንድ ተቀባይነት ማግኘት አስፈላጊ ነገር ነው። እኔም ባሳለፍኳቸው የአገልግሎት ዓመታት እግዚአብሔር ከሰጠኝ የማስታረቅ ጸጋ ባሻገር በተጋጩ ወገኖች የሰጠኝ ሞገስ በጣም ያስደንቀኛል። በቤተ ክርስቲያንም ሆነ በቤተሰብ ደረጃ የተቀበልኳቸው የማስታረቅ አደራዎች ሁሉ በሰላም ተጠናቅቀው ሳይ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ።

እኔ አዋቂ ሰው አይደለሁም። እግዚአብሔር ግን የማስታረቅ ጸጋውን ሰጥቶ ተጠቅሞብኛል። እናም የተጣሉን እንዳስታርቅ ጥበብ እና ማስተዋልን ጨምሮ በእነርሱ ዘንድም ሞገስን ሰጠኝ።

ሁል ጊዜ የማስታረቅ አገልግሎት በምሰጥበት ወቅት እግዚአብሔር የሰጠኝ ትልቅ ጥበብ፦ በመጀመሪያ ሦስት ዋና ጥያቄዎችን ለሁለቱም ወገኖች አቀርባለሁ። 1ኛ. የጠቡ መነሻ ምን እንደሆነ እና ከጠቡ በፊት ስለነበረው ሁኔታ፤ 2ኛ. ጠቡ ከተፈጠረ በኋላ የተጋጩት ወገኖች በምን ዓይነት ሁኔታ ውስጥ እንዳሉ፤ 3ኛ. ወደ ፊት ምን እንዲሆን እንደሚፈልጉ ጠይቄ ማስታወሻ እይዛለሁ። በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ትልቅ ማስተዋል ስለሰጠኝ ጉዳዩን በምሰማበት ወቅት ፈጽሞ አስተያየት አልሰጥም።

ከዚያ መደረግ ያለበትን ነገር ውሳኔ ለመስጠት ሳይሆን ለማስረዳት እሞክራለሁ። "እናንተ በዚህ አቅጣጫ ብትሄዱ ነገሩ እንዲህ ይሆናል። በዚያ ብትሄዱ ግን እንደዚህ ነው የሚሆነው።" እያልኩ ለማሳመን ጥረት አደርጋለሁ። ከዚያም የውሳኔ ሃሳብ ላይ ሳንደርስ እንዲያስቡበት እድል ሰጥቼ በቀጠሮ እለያያለሁ። በዚህ ጊዜ ከአንዱ ወገን የሰማሁትን ጨርሶ ለሌላው አልነግርም። አስታራቂ ፈጽሞ ለአንዱ መወገን የሌለበት ሲሆን የግድ መካከለኛ ሆኖ ነው ነገሩ ማለቅ ያለበት። እኔ ሁል ጊዜ የእርቅ ኃላፊነት ስቀበል በቡድንም ሆነ በግል ይህንን አቅጣጫ ነው የምከተለው። የአስታራቂዎች ቡድን ከሆንንም በመጀመሪያ በጋራ የምንከተለውን አቅጣጫ እንወስናለን። ብዙ ተወያይተን በጋራ ተማክረን ከጨረስን በኋላ በተስማማንበት አቅጣጫ የእርቁን ሂደት እንቀጥላለን።

እርቅ በአስታራቂዎች ስምምነት ካልተካሄደ ጥፋት ያስከትላል። ለምሳሌ የከምባታ እና ሃዲያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን መሪዎች አቶ ዳንኤል ከሚባል የዚያ ጽሕፈት ቤት የልማት ኃላፊ ጋር ተጣልተው ችግሩ መንግስት ድረስ ሄዶ ነበር። በኋላም የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን መሪዎች የነበሩት እነ ዶ/ር ተስፋዬ ያዕቆብ እኔን ሰብሳቢ አድርገው ከተለያየ ቦታ የመጡ ሰባት ሰዎችን የያዘ የአስታራቂ ቡድን ተደራጅና እንድናስታርቅ ተመደብን። ሁላችንም በጉዳዩ ላይ መረጃ ሰብስበን ከጨረስን በኋላ እግዚአብሔር ማስተዋል ሰጠኝ እና እያንዳንዳችን ለየብቻ የየራሳችንን የውሳኔ

ሃሳብ ይዘን እንድንመጣ ሃሳብ አቅርቤ በቀጠሮ ተለያየን። ስንመጣ የሁላችንም ሃሳብ አንድ ሆነ። ነገር ግን ከእኛ መካከል አንዱ ጉዳዩን ወደ አንድ ወገን ለመውሰድ ይሞክር ነበር። በመጨረሻም እርሱንም በማሳመን በአንድ ሃሳብ ተስማምተን ወሰንን።

በመጨረሻም የተጣሉትን ወገኖች ጨምሮ የወከሉንን የዋና ጽሕፈት ቤት እና የከምባታ እና ሃዲያ አውራጃ መሪዎች እንዲገኙ አድርገን ውሳኔያችንን አሳወቅን። በዚህ ጊዜ አንድ ትልቅ የቤተ ክርስቲያን መሪ ተነስቶ "ይህንን ውሳኔ ያመጣችሁት ትልቅ ውቅያኖስ በዋና አቋርጣችሁ ነው። ውሳኔአችሁ ትክክል ነው፤ እንቀበላለን" አለ። ሌላ ሰው ግን ተነስቶ ነገሩን ተቃውሞ እንደገና ጥሬ አደረገው። በዚህ ጊዜ እኔ ተነስቼ "ከዚህ በኋላ ከዚህ ጉዳይ ጋር ተያይዞ ለሚደርሰው ችግር ለእግዚአብሔርም ለቤተ ክርስቲያንም ተጠያቂ አንተ ነህ" አልኩትና ነገሩ ሳይቋጭ ተመለስን።

በኋላ እኛ በሌለንበት ውሳኔውን እንዲያስፈጽሙ ሌሎች ተላኩና አቶ ዳንኤል ከዚያ እንዲወጣ ተደረገ። ከዚያ በኋላ በዱራሜ እያበበ የነበረው የልማት ሥራ ሁሉ ተመልሶ በማሽቆልቆሉ ግቢውም ምድረ በዳ ሆኖ ቀረ። ከዚህ ሁሉ በኋላም የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪዎች እኛን ይቅርታ ሊጠይቁን ጠሩን።

በሌላ ጊዜ ደግሞ በሾኔ አምቡርሴ በምትገኝና ላሎ በምትባል አንዲት የቃለ ሕይወት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የእርስ በእርስ ክፍፍል ተፈጥሮ ነበር። በመጀመሪያ ያቺ ቤተ ክርስቲያን የተተከለችው በአንድ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ ደጅ ነበር። እናም ቤተ ክርስቲያኒቱ አድጋ ስለጠበበች ሌላ ሰፊ ቦታ ላይ የቤተ ክርስቲያን ሕንፃ ለመገንባት ገንዘብ ሲያሰባስቡ ቆዩ እና በመሃል ሰዎች ሽማግሌውን "አንተ በሕይወት እያለህ ቤተ ክርስቲያን ከአንተ ደጅ እንዴት ተነቅላ ትወሰዳለች?" አሉት። ሰውየው እና የተወሰኑ የእርሱ ወገኖች የቤተ ክርስቲያን ንብረት የሆኑትን ወንበሮችን፣ ሙዚቃ መሣሪያው ... እንዳይወጣና ወደ አዲሱ ሕንጻ እንዳይሄድ የድሮውን ሕንፃ ቆልፈው አገዱ። ጉዳዩ ክፍለ ማኅበር ጽሕፈት ቤት ቀርቦ እንዲሰጡ ቢወሰንባቸውም አሻፈረን አሉ፤ ከዚያ ጉዳዩ ኅብረት ጽሕፈት ቤት፣ ቀጣና ጽሕፈት ቤት እና ዋና ጽሕፈት ቤት ቢደርስም ሰዎቹ የተወሰነባቸውን ተመሳሳይ ውሳኔ አናከብርም አሉ። ከዚያም የአዲሲቱ አጥቢያ ሰዎች ጉዳዩን ወደ ፍርድ ቤት ወሰዱ። ነገሩ ለቤተ ክርስቲያንም መሰደቢያ ሆነ።

አንድ ቀን ከአቶ ኩርሴ ሽፈና ጋር ዱራሜ ባለው የቃለ ሕይወት የሚስዮናውያን ማሠልጠኛ ለማስተማር በሄድንበት ወቅት የተከሰሰው ሰውዬ መጥቶ አቶ ኩርሴን ያነጋግር ነበር። እኔ ግን ጉዳዩን ሰምቼ ስለነበር ከሰውዬው ጋር መነጋገር እና የሚለውን መስማት አልፈለግሁም።

ከተወሰነ ጊዜ በኋላ አዲስ አበባ እያለን አቶ ደምሴ ማዴና እኔ በዚያች ቤተ ክርስቲያን ጉዳይ የማስታረቅ ሥራ እንድሠራ ጠየቁኝ። እኔም ነገሩ በተለያየ የቤተ ክርስቲያኒቱ እርከን እየታየ ሲወሰን የቆየ ስለሆነ ባበቃ ጉዳይ ውስጥ ጣልቃ መግባት እንደማልችል ነገርኩት። ሆኖም ደምሴ እኔ ጉዳዩን እንድይዘው እና እነርሱ እንደሚጸልዩልኝ ነግሮኝ

የማስታረቅ ሥራ እንድሠራ ግድ አለኝ። እኔም "እሺ ጸልዩ መልስ እሰጣለሁ" ብዬ ወደ ጸሎት አመራሁ። እግዚአብሔርም እንደሚሠራ ስለተናገረኝ የማስታረቅ ሥራ ለመሥራት ተነሳሁ። ከዚያም ከመጋቢ ዮሐንስ ባሳና ጋር ሆነን ወደ ሸኔ አመራን።

በመጀመሪያ የአዲሲቱን አጥቢያ መሪዎች ይዘናቸው ወደ ቀድሞው አጥቢያ እንድንሄድ ስንጠይቃቸው "ይደበድቡናል አንሄድም" አሉ። እኛም "ክርስቲያኖች ሰው ይደበድባሉ? እንደዚያ ከሆነ እኛም አብረን እንደበደባለን፤ ኑ እንሂድ" ብያቸው ተያይዘን ሄድን። ከዚያም ከሁለቱም ወገን ሰዎች ይዘን አብረን ተንበርክከን ጸለይን፤ ቃሉንም ሰማን። በመጨረሻም ደግመን ጸለይንና እኔና ዮሐንስ ከላይ የተጠቀሱትን ሦስቱን ጥያቄዎች ለየብቻ አድርገን ጠየቅናቸው።

ሁለቱም ወገኖች የየራሳቸውን ሃሳብ ሰጡ። የአዲሲቱ አጥቢያ ሰዎች ሽማግሌው እንደ ቀድሞው ሁሉ በአዲሱ አጥቢያም መጋቢ ሆኖ ያገልግል፤ የጸሎት ቤቱን ቁልፍም ይያዝ ብለው ተስማሙ። የሽማግሌው ወገኖች ግን እዚያው የቀድሞው አጥቢያ እንቀጥላለን ብለው እምቢ አሉ። እኔም "በመጀመሪያ ለአዲሱ ጸሎት ቤት መሥሪያ ቦታ እንዲፈለግና ሕንፃ እንዲገነባ አልተስማማችሁም ነበር ወይ? በጋራስ ገንዘብ አልሰበሰባችሁም ወይ? አልኳቸው።" "አዎን ተስማምተን ነበር" አሉ።

"ታዲያ ያንን ሃሳብ አሁን ስታፈርሱ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ እና የቤተ ክርስቲያን አሠራርን በጠበቀ መንገድ ነው ወይስ በሥጋዊ አሠራር ነው?" አልኳቸው። በኋላም እኛ ተነጋግረን የውሳኔ ሃሳብ ይዘን እንመጣለን ብለን ቀጠሮ ተሰጣጥተን ተለያየን። በዋና ጽሕፈት ቤትም እኔና ዮሐንስ ባሳና ከአቶ ኩርሴ ሽፈና ጋር ሆነን የቀደሞው ሕንፃ የጸሎት ቤት፣ የአስተዳደር፣ የወጣቶች፣ የሴቶች ... የአምልኮ ቦታ እንዲሆን ወሰንን።

በቀጠሮአችን ዕለት ሄደን ውሳኔውን ስንነግራቸው አሁንም አዲሶቹ በደስታ ሲስማሙ የሽማግሌው ወገኖች ግን በድጋሚ ተቃወሙ። እኔም ሁለት ሰዓት ሙሉ ቆሜ የሚሄዱበት መንገድ አደገኛ እንደሆነ በሰፋት አስረዳኋቸው። በመጨረሻም ሽማግሌውን "ግን እርስዎ ስለዚህች ቤተ ክርስቲያን እድገት እና መስፋፋት ጸልየው ነበር ወይ?" ብዬ ስጠይቃቸው "አዎ" አሉ። "ታዲያ ይህ የጸሎትዎ መልስ ነው ወይስ በተቃራኒው ነው?" አልኳቸው።

"የጸሎቱ መልስ ነው" አሉ።

"እና አሁን እርስዎ የጸሎትዎን መልስ እየተቃወሙ ነው ማለት ነው?" ስላቸው ሽማግሌው መልስ ሳይሰጡ ጸጥ አሉ። በዚህ ሁኔታ እየተነጋገርን እያለም በድንገት አንድ ወጣት ተነስቶ እኛን "አንድ ጊዜ እናንተ ውጡ ብሎ ሁላችንንም አስወጣ እና የሽማግሌው ወገኖች ብቻ ቀሩ። ያ ወጣት ለብቻው አስረዳቸው እና እንደገና መልሰው ጠሩን። በዕለቱ የእርቅ ቀን ነው ተብሎ የቤተ ክርስቲያን አባላት ሁሉ ተሰብስበው መጥተው ስለነበር፤ ሰው ሁሉ ተመልሶ ከገባ በኋላ "እግዚአብሔር ምህረት ያድርግልን፤ ጸልየን እግዚአብሔር የሰጠንን የጸሎት መልስ መልሰን ተቃውመናል፤

እናንተም ምህረት አድርጉልን፤" ብለው "የእግዚአብሔርን ሥራ በመቃወማችን አዝነናል።" ብለው ስቅስቅ እያሉ በማልቀስ በንስሃ ወደ እግዚአብሔር ቀረቡ። በኋላም አንድ ላይ የሚቀላቀሉበትን ቀጠሮ ሰጠን። በቀጠሮው ዕለት ሽማግሌው ከፊት፣ ዘማሪዎች ቀጥለው ጉባኤው ከኋላ የቤተ ክርስቲያን ዕቃዎችን ተሸክመው በዝማሬ እና በደስታ ወደ አዲሱ ሕንፃ ተዛወሩ። ያ ሥነ-ሥርዓት በቪዲዮ ተቀርጾ ቢሆን ኖሮ እንዴት ድንቅ ነበር!! ብቻ በጣም ደስ በሚል ሁኔታ በብዙ ደስታ እና እልልታ እርቁ በመካናዱ እግዚአብሔርም ከበረ።"

በ1991 ዓ.ም ደግሞ እኔ እና ወንድም አየለ የቱራ ለሥልጠና ሲዳማ ሄደን ነበር። እኔ በምሄድበት ቦታ ሁሉ ትምህርት፣ ሥልጠና ወይም ስብከት ሳልጨርስ ችግር በተለይ የጥል ወሬ መስማት አልፈልግም። ምክንያቱም ያ ወሬ አዕምሮዬን ይዞ ከማስተምረው ትምህርት ጋር እንዲደባለቅብኝ ስለማልሻ ነው። በሚማረው ሕዝብ መካከልም የዚያ ወሬ ደጋፊ አሊያም ተቃዋሚ ስለማይጠፉ ለእነርሱም ችግር ይሆናል። በዚህ ጊዜ ግን አንድ ሰው መጥቶ ተው አትንገረኝ ብለውም እምቢ በማለቱ ሲዳማ ውስጥ ችግር ተፈጥሮ አራት ክፍለ ማኅበራት እንደቱበጣበጡና በዚህም ሳቢያ 40 ቤተ ክርስቲያናት ተዘግተው ጉዳዩ ወደ ፍርድ ቤት እንደሄደ ሁሉ ነገረኝ። ተው ብለውም አልሰማ ብሎ ነገረኝና እኔንም በጥብጦኝ አረፈው። "40 አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት ተዘግተው እኔ ምን ጤና አገኛለሁ?" እያልኩ ነገሩን በብስጭት እያመላለስኩ ሳሰላስለው ጨጓራዬም ተቃጠለ እና ሕመሙ ከልክ በላይ ሆነብኝ፤ አመመኝ። በሄድንበት ዕለት እንኳን ለማስተማር ስላልቻልኩ አቋርጬ በማግስቱ በአውቶብስ ወደ አዲስ አበባ ተመለስኩ።

ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ይርጋ ዓለም አቅራቢያ ባለ ክፍለ ማኅበር ሥልጠና ልሰጥ ሄድኩ። ከዚያም ቅዳሜ ማታ ይርጋ ዓለም የስብከት አገልግሎት ነበረኝ። በሌላ ቦታ ደግሞ ተከፍለው የወጡት ወገኖች በዚያው በይርጋ ዓለም ትልቅ ኮንፍራንስ ነበራቸው። ሄጄ ኮንፍራንሱን ብቀላቀል የሆነ ነገር እንዳደርግ ይጋብዙኛል፤ እምቢ ብል ደግሞ ተቃዋሚ ነው እባላለሁ፤ እሺ ብልም የእነርሱ ደጋፊ እባላለሁ። ስለዚህ ዝም ብዬ ቀኑን በክፍሌ አሳለፍኩ እና ኮንፍራንሱ ከተጀመረ በኋላ ቀስ ብዬ ሄጄ መሪዎቹን አነጋገርኳቸው። ቁጭ እንዲሉ አድርጌ በደንብ ተነጋገርን። በቦታው ደግሞ ለሁለት የተከፈሉት ሁለቱም ወገኖች ስለነበሩ ለየብቻ ሁለቱንም ቡድን አነጋገርኩ እና ጉዳዩን ወደ ሌላ ከሚወስዱ ዋና ጽሕፈት ቤቱ እንዲገባበት ጠየቅኳቸው። እግዚአብሔር ትልቅ ሞገስ ሆነኝና ተስማሙ።

በመጨረሻም እኛ አንዱ ወገን በአንድ ሰው ላይ የጻፉትን የክስ ደብዳቤ ወደ ጎን አድርገን ሁሉንም ሰብስበን አነጋገርን። ከዚህ በፊት ሰባት ያህል የቤተ ክርስቲያኒቱን ትልልቅ ሰዎች እናነጋግርም ብለው መልሰው የነበረ ቢሆንም ለእኔ እግዚአብሔር በፊታቸው ሞገስ ሰጠኝ እና ተሰብስበን ተነጋገርን። በጉዳዩ ላይ ክርር ያለ አቋም የያዘ አንድ ብርቱ መንፈሳዊ ሕይወት የነበረው ትልቅ የቤተ ክርስቲያን መሪ ነበረ። ያ ሰው ቃሉ ሲሰበክና ሲጸልይ መንፈስ ቅዱስ ተናገረው፤ ተነስቶ "ተሳስተናል" አለ። በክፍፍሉ የተዘጉት አርባ አጥቢያዎች ሊከፈቱም ቀጠሮ ተያዘ። ከዚያ አርፌ የሚባል አጥቢያ

ባለበት አካባቢ ባለ ሰፊ ሜዳ ላይ ፕሮግራም ተዘጋጅቶ ሕዝቡ ሁሉ እዚያ ተሰበሰበ። እኔም እግዚአብሔር ሞገስ ሰጥቶኝ ብቻዬን ሄጄ መልእክት አቀረብኩ። ከዚያም የተሰበሰበውን ሕዝብ "አንድ መሆን ነው ለእግዚአብሔር ክብር የሚሆነው ወይስ መከፋፈል?" ከዚያም "እስከአሁን በነበረው መለያየት እግዚአብሔር ከብሯል፤ እኛም ተባርከናል፤ ግጭቱ ጠቅሞናል የምትሉ እጃችሁን አውጡ" አልኩና ጠየቅኋቸው፤ ሁሉም ዝም አሉ። "የእስካሁኑ መለያየት ጎድቷችኋል። በአንድነት ስንሆን ቤተ ክርስቲያን ታድጋለች፤ እግዚአብሔር ይከብራል የምትሉ እጃችሁን አንሱ?" አልኩ፤ እጃቸውን ሲያነሱም "ተነሱና ቁሙ። ... ተቃቀፉ።" ስል ሕዝቡ በእምባ እየተራጨ እርስ በእርስ መተቃቀፍ በመጀመሩ ትልቅ ትርምስ ሆነ። በዚህ ዕለት የነበረው ትዕይንት በቪዲዮ ተቀርጾ ቢቀመጥ ኖሮ ብዬ እመኛለሁ።

ይሁንና በሲዳማ የነበረው ችግር በዚያው ተፈትቶ አልቀረም፤ ወዲያውኑ አንዱ ኅብረት ተነስቶ ጥያቄ አንስቶ ሌላ ጥል ተፈጠረ። እኔም እንደገና ከዋና ጽሕፈት ቤቱ አቶ ማሞ ከሚባሉ የሲዳማ ሰው ጋር  ለእርቅ ተልኬ ነበር። ሆኖም የተፈጠረውን ልዩነት በሰላማዊ መንገድ ስለመፍታት ስናገር አንዱ ተነስቶ  እኔ የተናገርኩትን ተቃውሞ በሲዳምኛ በኃይል ተናገረ። እኔም "ይህ መንፈሳዊ አካሄድ ነውን? መጽሐፍ ቅዱስስ የሚደግፈው ነውን?" ብዬ አልቅሼ ተመልሼ ተቀመጥኩ። በዚያው እርቁ ሳይካሄድ ተለያየን።

ሆኖም ከዚያ በኋላ በሲዳማ ምድር ከወላይታ ጋር ከፍተኛ አለመስማማት ተከሰተ። ከመንግስት ጋር ቅራኔ ውስጥ ገቡ፤ ረኃብ በምድሩ ላይ ሆነ፤ በዚህ ጊዜ በ2001 ዓ.ም በነሐሴ ወር እኔን፣ አቶ ማሞን እና ወ/ሮ አልያስን ጠርተው ሕዝቡ ሁሉ ተንበርክኮ "በድለናል ማሩን!" ብለው ይቅርታ ጠየቁን። እኛም ለተንበረከከው ሕዝብ ጸልየን እግዚአብሔር አገራቱን እንዲባርክ ጠይቀን ተመለስን።

በዚህ መልኩ በብዙ ቦታ በተለይ በዋና ጽሕፈት ቤቱ በኩል ተልኬ እየሄድኩ በርካታ እርቆች የተካሄዱ ሲሆን በቦቢቾም በተደጋጋሚ ችግር እየተፈጠረ ብዙ ጊዜ ያህል ተመላልሼ አስታርቄአለሁ።

አንድ ጊዜ ዱራሜ ያለው የቀጣና ጽሕፈት ቤት እና አንድ ክፍለ ማኅበር ተጣልተው የክፍለ ማኅበሩ መሪዎች በተደጋጋሚ ለሙግት ወደ ዋናው ጽሕፈት ቤት ይመላለሱ ነበር። የዚያ ክፍለ ማኅበር ሰብሳቢ የኔ የቅርብ ወዳጄ የሆነ ጥሩ መንፈሳዊ ሰው ሲሆን ከጓደኞቹ ጋር ወደ ጽሕፈት ቤት ሲመላለሱ አለቆችን ለመጠበቅ የሚቀመጡት በኛ ቢሮ ትይዩ ነበር። አንድ ቀን ደጅ ከተቀመጡበት ጠርቼ አምስቱንም እኛ ቢሮ ውስጥ አስገብቼ አነጋገርኳቸው። የነበራቸውን ጉዳይ ከሰማሁ በኋላ ወደ ዋና ጸሐፊው ዶ/ር ተስፋዬ ሄደን ጉዳዩን እኔ እንድይዘው ስጠይቀው እርሱም መርቆ ሰጠኝ። ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን እና እንደገና በእነዚህ ሰዎች ፊትም ሞገስ ሆኖኝ ከቀጣናው ጋር ታርቀው ጥያቄአቸውን አንስተን ለሙግት ከመመላለስ እንግልት አረፉ።

እግዚአብሔር የሰጠኝ የማስታረቅ የጸጋ ስጦታ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብቻም የተገደበ አልነበረም። የማስታረቅ ጸጋ ቤተ ክርስቲያንን ብቻ ሳይሆን ቤተሰብንም ከመፍረስ ማዳን የሚያስችል ነው።

በጌጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ወንጌላዊ በነበርኩበት ዘመን አንድ ጊዜ እንዲህ ሆነ። ከቤተ ክርስቲያን አገልጋይ መሪዎች አንዱ የሆነ ወንድማችን ከባለቤቱ ጋር ተጣልተው እርሱ ዕቃውን ሸክፎ ከቤት መውጣቱን ጎረቤቱ አቶ አዱኛ ደውሎ ነገረኝ። በኋላም ያለበትን እንዲያሳየኝ ተነጋግረን ያ ወንድም ያለበት ቤት ድረስ ሄድኩ። እንደተለመደው ሦስቱን ጥያቄዎቼን አቀረብኩለትና እርሱም መለሰ። በስተመጨረሻም "ከዚህ በኋላ ምን እንዲሆን ትፈልጋህ?" ስለው "እኔ እንዲህ መኖር እችላለሁ።" አለ። እኔም "እንደዚህ ልትኖር ትችላለህ፤ ነገር ግን የዚህ አይነቱ ኑሮ ውጤቱ ምን ይሆናል? በአንተ፣ በባለቤትህ፣ በልጆችህ ሕይወት ዙሪያ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ባለህ ኅብረት እና እስከአሁን ከእርሱ ጋር በኖርከው ሕይወት ላይ ግን የሚያመጣው ውጤት አልታየህም ወይ?" አልኩት። ብዙ ከመከርኩት በኋላም "አሁን እዚህ ትኖራለህ ወይስ እዚያ ከእግዚአብሔር ጋር በእግዚአብሔር ጸጋ ሁሉን እየቻልክ አብረህ ከቤተሰብህ ጋር ትኖራለህ?" አልኩት። ከዚያም "ሁለተኛ ፊትሽን አላይም፤ ከዚህ በኋላ እዚህ ቤት ሬሳዬ እንኳን አይመለስም!" ብሎ ወደ ወጣበት ቤት ተያይዘን ሄድን። ስንደርስ እርሷም በግቢአቸው ውስጥ ባለና የባህር ዛፍ ችግኞች ያሉበት ጥሻ ውስጥ እየጸለየች ከነበረችበት ወጥታ ለ15 ደቂቃ ብቻ ቆም ብለን ተወያይተን ታረቁ። እርሷ በመኪና አደጋ እስከሞተችበት ጊዜ ድረስም ሳይለያዩ በፍቅር ኖረዋል።

በአንድ የገጠር ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ደግሞ ሰባት ልጆች የነበሯቸው ባልና ሚስቶችት ነበሩ። አንድ ጊዜ ሴትየዋ ከሌላ ወንድ ጋር በዝሙት ኃጢአት በመውደቋ ባሏ ለቤተ ክርስቲያን ከሰሳት። ቤተ ክርስቲያኒቱም ጉዳዩን ወደ ክፍለ ማኅበር መርታው የክፍለ ማኅበሩ መሪዎች ጉዳዩን አይተው ባልና ሚስቱ እንዲለያዩ ወሰኑ። ባልና ሚስቱ እስከዚያ ጊዜ ድረስ ጥሩ ግንኙነት የነበራቸው በቤተ ክርስቲያንም ጥሩ ስም የነበራቸው ነበሩ። በድንገት ግን ባል ለሥራ ወደ ሌላ ቦታ ሲሄድ እርሷ የዚያው ቤተ ክርስቲያን አባል ከሆነ ክርስቲያን ጋር በዝሙት ወደቀች። በቤተክርስቲያን ውሳኔ መሠረትም ያ ቤተሰብ ሊፈርስ ሆነ።

እኔ ይህን ስሰማ አገሩ ምንም ሩቅ ቢሆንም የ4 ሰዓት መንገድ ተጉዤ ሄድኩ። ከዚያም ሚስቱን ከሰሶ እንዲተዋት በቤተ ክርስቲያን የተፈረደለትን ተበዳይ ሄጄ አነጋገርኩት። "አሁን ሚስትህን ፈትተህ ሰባት ልጆች ይዘህ ከዚህ ከበደለህ ሰው ጋር እንዴት በአንድ ቤተ ክርስቲያን መኖር ትችላለህ። ሚስትህን አጥተህስ እነዚህን ልጆች ስታሳድግ በብቸኝነት ያንተና የእነርሱስ ሕይወት አይጎዳም ወይ?" ብዬ ጠየቅሁት። "ከዚህ ሁሉ ጣጣ እርሷን ይቅር ማለት ይቀላል ወይስ ይህን ሁሉ ስቃይ መቀበል?" ስለው "እርሷን ይቅር ማለት ይቀላል።" ብሎ ይቅርታ ለማድረግ ተስማማ።

እኔም ወደ ቤተ ክርስቲያኒቱ መሪዎች ሄጄ ጉዳዩን ነገርኳቸው። እነርሱንም "ወደፊት ሰውየው እንዴት ይኖራል ብላችሁ ወሰናችሁ? ከመለያየት ማስታረቅ አይሻልም?"

ስላቸው በነገሩ ተስማምተው "እግዚአብሔር ነው አንተን የላከልን።" ብለው እኔን ባርከው ከክፍለ ማኅበሩ ጋር ተነጋግረው ሰዎቹ ሁሉ ይቅርታ ተጠያይቀውና ቤተ ክርስቲያንንም ይቅርታ ጠይቀው ጉዳዩ ተዘጋ። ያ ሊፈርስ የነበረ ቤተሰብ ከመፍረስ ድኖም ባልና ሚስቱ እስከ ዛሬ ድረስ አብረው ኖረው ልጆቻቸውን ድረው የልጅ ልጆች በማፍራት አብረው እስከሽምግልና ዘልቀዋል። በኔ አልፎ የብዙዎች ሕይወት እንዲታደስና በይቅርታ እንዲለመልም ያደረገው ለእኔም "የሚያስተራርቁ ብጹአን ናቸው" ብሎ ይህንን ክቡር ተስፋ ወራሽ ያደረገኝ ታማኙ አምላካችን እግዚአብሔር የተባረከ ይሁን!!

# 5.ጸሎት

እምስተኛው የኔ የአገልግሎት ጸጋ ጸሎት ነው። በእውነቱ ጸሎት ለአገልግሎት ብቻ ሳይሆን የክርስቶስ ደቀ መዝሙር የሆነ ሁሉ ጌታን ከተቀበለበት ዕለት አንስቶ የሕይወቱ ዋና ነገር እና የዕለት ተዕለት ሥራው አድርጎ ሊይዘው የሚገባው ነው። እኔም ክርስቶስ ኢየሱስን እንዳመንኩ ገና በደንብ ስላገኘሁት አዲስ ሕይወት ሳልማር ከቤተሰቤ ባጋጠመኝ ስደት ወቅት ጌታ ጸሎትን በመንፈሱ አማካኝነት አስተማረኝ። ከዚያ ጊዜ አንስቶም ጸሎት ለግል ሕይወቴ አስፈላጊና ዋና ነገር ሆኖ ቀረ። በጸሎት ኃይል ብዙ መልስ እንደሚገኝ ክርስቶስ ኢየሱስም በግል ሕይወቴ ደጋግሞ አሳይቶኛል።

እግዚአብሔር በጸሎት ፊቱ ስቀርብ የአገልግሎት በር ከፈተልኝ። ለመጀመሪያ ጊዜ በወንጌል ለባሲነት ወደ ጌዴኦ እንድሄድ የተጠራሁት በብዙ እምባ በጸሎት በእግዚአብሔር ፊት በቀረብኩበት ጊዜ ነበር። በጸሎት እግዚአብሔር ያጋጠሙኝን አስከፊ ፈተናዎች አሻገረኝ። ልጄ ብሔራዊ ውትድርና ሊወሰድ መጥሪያ በደረሰው ጊዜ እግዚአብሔር ጸሎቴን ሰምቶ የመውጫ መንገዱን አሳየኝ። በጸሎት ሕይወቴ ስጨነቅ እረፍትን ሰጠኝ። ባለቤቴ ታደለች ሞታ በእርሷ ቀብር ዕለት በሌሊት ከእርሷ ሞት የተነሳ በሃዘን እያለቀስኩ ስጸልይ እግዚአብሔር እንደገና እንደሚያለመልመኝ አሳየኝ። ይኸው ባለፉት ዓመታት ለምልሜም ብዙ ፍሬ አይቻለሁ።

በክርስቶስ ካመንሁ በኋላ በተጨነቅኩበት ሰዓት መንፈስ ቅዱስ እንድጸልይ ካስተማረኝ ጊዜ አንስቶም ጸሎት የሕይወቴ ዋና ነገር ሆነ። እስከ ዛሬ በሌሊት ለጸሎት ወደ እግዚአብሔር እቀርባለሁ። ሁል ጊዜ በምሽትም ቤተሰቤ በሙሉ ተሰብስበም ቃሉን አጥንተን እንጸልያለን። እኔና ባለቤቴ ለብቻችን ደግሞ ሁል ጊዜ ወፎች ሳይቀድሙን ማለዳ ተነስተን በእግዚአብሔር ፊት በምስጋና እንቀርባለን፤ ቃሉንም እናጠናለን።

ይህ የጸሎት ትጋቴ ለኔ እና ለአገልግሎቴ ብቻ ይደረግ የነበረ አይደለም። እግዚአብሔር በችግሮች ሁሉ ላይ እንድጸልይ አስተምሮኝ በአገልግሎት ዘመኔ ሁሉ ከኔ እና ከአገልግሎቴ ባሻገር ለቤተሰቤ፣ ለቤተ ክርስቲያን፣ ለማገለግላቸው ወገኖች፣ ለአገሬ እና ለመሪዎቿ፣ ለምሄድበት እና ለምረግጠው ምድር ሁሉ እጸልይ ነበር። በዚህ የጸሎት ሕይወት አልፎም እግዚአብሔር ብዙ መልሶችን ሰጥቶኛል። የጸለይኩት ጸሎት ከዘመናት በኋላ ፍሬ ሲያፈራ እና የብዙዎችን ታሪክ ቀይሮ አስደናቂ ለውጥ ሲያመጣ እያየሁ እግዚአብሔርን አመስግኛለሁ።

እግዚአብሔር በጸሎት ከሰጠኝ ድሎች መካከል ጥቂቶቹን ልተርክላችሁ። በጌጃ አጥቢያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ በነበርኩበት ዘመን በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት አስተምረው የነበረ አንድ አማረ ኃ/ጊዮርጊስ የሚባል ወንድም ነበር። አማረ በጣም ትጉህ እና ጥሩ ክርስቲያን ሲሆን በሥራውም ሆነ በመልካም አገልጋይነቱ የተመሰከረለት እና ዶክተሮች እንኳን እንደ እርሱ አያክሙም የሚባልለት በጥቁር

አንበሳ ሆስፒታል የሚያገለግል ነርስ ነበር። አማረ በዚያ ዘመን አስር ልጆች ስለነበሩት በሚያገኘው አነስተኛ ደመወዝ እየኖረ ፈጽሞ ቤት ለመሥራት ሳያስብ ሰፊውን ቤተሰቡን ይዞ ከጌጃ በቅርብ ርቀት ላይ በጠባብ የኪራይ ቤት ውስጥ ይኖር ነበር። እኔ የእርሱን የኑሮ ሁኔታ በማየት እግዚአብሔር አንድ ቀን ይመልሳል በሚል እምነት "እግዚአብሔር ቤት እንዲሰጣችሁ እንጸልይ" እለው ነበር። እርሱ ግን የራሱን ሁኔታ በማየት "እንጸልይ" ስለው ይቀልድ ነበር።

ከብዙ ዓመታት በኋላ በዚህ በ2008 ዓ.ም አማረ እኔ ቤት መጣ። በወቅቱ እኔጋ የመጣበት ዋና ምክንያት ሴት ልጁን ሊድር ሰርግ ደግሶ ሊጠራኝ ነበር። የሠርጉ የመጥሪያ ካርድም ሆነ እርሱ የተረከልኝ የልጁ እና የምታገባው ባል ሁኔታ አስደናቂ ነበር። ከዚህም ባሻገር ሠርጉ ሙሽሮች በረጅም ሊሞዚን ሚዜዎች አጠር ባለ ሊሞዚን ሆነው የተጓዙበት፣ ድል ያለ ድግስ ተደግሶ የተበላበት፣ አስደናቂ የወንጌል መልዕክት የቀረበበት እጅግ የደመቀ ሠርግ ነበር።

አማረ ገና ወደ እኔ ቤት ሲመጣ እና ልጁን ሊድር እንደሆነ ሲነግረኝ አሁን ቤተሰቡ ስላለበት የተባረከ ሁኔታም አጫወተኝ። ዛሬ ልጆቹ አሜሪካን እና በሌሎች ሃገራት የሚኖሩ ሲሆን አንድ ወንድ ልጁ ለቤተሰባቸው በጣም ጥሩ ቪላ ቤት ቤቴል እየተባለ በሚጠራው አካባቢ እንዲሠራላቸው ነገረኝ። እኔና አማረ ያኔ ጌጃ አጥቢያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን እያለን እኔ ቤት እንዲያገኙ የጸለይነውን ጸሎት አስታውሰን ጌታን አመሰገንን። እግዚአብሔር ጸሎታችንን ሰምቶ ስለመለሰም በእግዚአብሔር ፊት የምስጋና እምባ እያነባን ወደ ፊቱ ቀረብን።

ሌላው እግዚአብሔር በኔ ውስጥ ባስቀመጠው የጸሎት አገልግሎት ጸጋ የተገለጠበት ወቅት የጌጃ ቃለ ሕይወት በደርግ ልትዘጋ የመጨረሻ ምዕራፍ ላይ ደርሳ የነበረችበት ጊዜ ነው። ያኔ አንድ ቅዳሜ ቀን ቤተ ክርስቲያኒቱ እንደምትዘጋ ማረጋገጫ እንዲሆን የቀበሌ አመራሮች ቤተ ክርስቲያኒቱ ግቢ ድረስ መጥተው የተለያዩ እምነትን የሚያጥላሉ መፈክሮችን ጻፉ። በዚያ ዕለት ምሽትም እኔ ወደ ቤቴ ሄጄ "እግዚአብሔር ሆይ የጌጃ ቃለ ሕይወት ሕዝብ አንተን ምን በደለ? እንዴት ቤተ ክርስቲያን እንዲወሰድባቸው ትፈቅዳለህ? እነርሱ በሙሉ ያንተ ናቸው። አንተ ግፈኛ ነህን?" እያልኩ ምሬት የተሞላበት ጸሎት ጸለይኩኝ። እግዚአብሔርም አዕምሮዬን የሚያሳርፍ መልስ ሰጠኝ።

በእርግጥ የጌጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ሕዝብ በዚያ ወቅት የእግዚአብሔርን ቃል ለመማር፣ በልዩ ልዩ የአገልግሎት ዘርፎች ገብቶ ለማገልገል በብዙ አቅጣጫ ፈቃደኛ የሆነ ሕዝብ ነበር። ቅዳሜ በቤተ ክርስቲን የሆነውን ያየ እና የሰማ የጌጃ ቃለ ሕይወት ሰው በሙሉም በየቤቱ ሲጸልይ አደረ። እኔም ሌሊቱን በጸሎት አሳልፌ ከጉጉት የተነሳ በ11:00 ሰዓት ገና ሰማይ እና ምድር ሳይላቀቅ ተነስቼ ወደ ጌጃ በእግሬ አመራሁ። ልክ በ12:00 ሰዓት ጌጃ መሠረተ ሕይወት ግቢ ስደርስ ሽመልስ ወዳጆ እና አቶ ብርሃኑ ደረሰ ተከታትለው መጡ።

እኛ እዚያ እያለንም ጓድ ተሰማ የሚባለው የቀበሌው ም/ሊቀመንበር ሰባት ወታደሮች አስከትሎ መጣና እንደገና ግቢው ውስጥ መፈከር መጻፍ ጀመሩ። እኛም ምንም አልተናገርንም። እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያናችን "እኔ የእሳት ቅጥር እሆናታለሁ ብሎናል እና እርሱ ቃሉን ያከብራል" ብለን ዝም ብለን የሚያደርጉትን አይተን ወደ ቤተ ክርስቲያኒቱ ምድር ቤት ሄደን መጸለይ ጀመርን። ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ሄዶ ግቢያችን የገባውን እስጊ ሁኔታ ወደ ጌታ እያቀረብን በእምባ ጸለይን። ሕዝቡም ሁኔታውን ለማየት እየመጣ ሰዓት እየረፈደ በሄደ ቁጥሩ ይጨምር ጀመር። ጸሎታችንንም በኃይል እየጸለይን ቆየን። በጸሎት ላይ እያለንም ከትንቢተ ዘካሪያስ መጽሐፍ ምዕራፍ 8 ላይ *"ስለጽዮን ታላቅ ቅንዓት ቀንቻለሁ .... በታላቅም ቁጣ ስለእርሷ ቀንቻለሁ ... "* የሚለውን ክፍል ሳነብብ ሕዝቡ በታላቅ ድምጽ አሜን ብሎ ጮኸ። ያ ቀን በጣም አስደናቂ የጸሎት ቀን ነበር። በዚያች ዕለት በነበረው ጸሎት 15 ሰዎች ጌታን ተቀብለው አመኑ። ነገሩ ለእኛም ከፍርኃት ይልቅ አስደናቂ ነበር። በኋላም እግዚአብሔር አስደናቂ ሥራውን በቤተ ክርስቲያናችን ቅጥር ግቢ ውስጥ በነበሩት የቀበሌ ሰዎች መካከል ይሠራ ጀመር። ከዚያም ቀጠልኩ እና "እግዚአብሔር ለጌጃ መሠረተ ሕይወት ቀንቻለሁ ይላል።" "ጌጃ መሠረተ ሕይወት እንደገና የአገልግሎት ቦታ ይሆናል ብሏል።" ስል ሕዝቡ "አሜን" ብሎ በታላቅ ድምጽ ተስማማ። ከሰዓታት የምልጃ ጸሎት በኋላ ስንወጣ በወታደር ተወርሮ የነበረው ግቢአችን ባዶ ነበር።

ለካስ እኛ ጸሎት ላይ እያለን ጌታ የአስጨናቂዎቻችንን ሃሳብ ደበላልቆት የቀበሌው ሊቀ መንበር እና ምክትሉ በሚወረሰው የእኛ ቤተ ክርስቲያን ንብረት ዙሪያ ሲከራከሩ ቆይተዋል። በኋላም የሁለቱ ሙግት ድብልቅልቅ ወዳለ ጸብ አምርቶ ሊጎዳዱ ሲደርሱ ቤተ ክርስቲያን ሊዘጉ እና እኛን ሊይዙ የመጡ ወታደሮች ሁለቱን ይዘው ወደ መጡበት ተመልሰዋል። በዚህ መልኩ እግዚአብሔር ተዓምራት ሠርቶ ቤተ ክርስቲያናችንን ከመወረስ ታደጋት። ከዚያ በኋላም ማንም ተመልሶ ወደ እኛ አልመጣም። እንደሰጠን የተስፋ ቃልም እግዚአብሔር ለጌጃ አጥቢያ የእሳት ቅጥር ሆኖአታል።

በቅርቡ በ2003 ዓ.ም ደግሞ በሻሾጎ ክፍለ ማኅበራት ኅብረት አዘጋጅነት በሚካሄድ የወንጌል ኮንፍረንስ ላይ ለማገልገል የቤተ ክርስቲያናችን ሚሲዮናዊ ከሆነው አበራ አየለ ጋር ወደ ቦኖሻ ሄደን ነበር። በጊዜው አገልግሎት የምሰጥበት ሰዓት ደርሶ ፕሮግራሙ ወደሚካሄድበት አዳራሽ ስንገባ በአዳራሹ ውስጥ 18 ሰው ብቻ ነበር የተገኘው። በዚህም በጣም ልባችን ተሰብሮ ቀደም ሲል መንፈሳዊ ጥማት የነበረው ሕዝብ ልብ መቀዝቀዙን በማየት አዘንን። ከዚህ በኋላም እኔና ባለቤቴ ሰላም አንድ ክፍል ውስጥ ገብተን ጌታ ይህንን የቤተ ክርስቲያን ሁኔታ እንዲለውጥ በእምባ ጸለይን።

ከዚያም በኋላ በጊዜው ለነበረው ጥቂት ሕዝብ ሐዋርያው ጳውሎስ በ2ኛ ቆሮንቶስ መጽሐፍ ምዕራፍ 4 ላይ ስለመሰልቸት እና መታከት ከአርብ እስከ እሁድ በነበሩት

ሦስት ቀናት አስተምሬ ወደ አዲስ አበባ ተመለስን፡፡ በጊዜው እኔና ሰላም ልባችን ተሰብሮ በጣም አዝነን ስለ ነበረው የመንፈሳዊ ሕይወት መቀዝቀዝ ጸለይን፡፡

ብዙም ሳይቆይ በ2005 ዓ.ም በሃዲያ ምድር ባሉ ገጠሮች ላይ የእሳት ቃጠሎ አደጋ ተከስቶ በርካታ የሳር ቤቶች ትቃጠሉ፡፡ ቃጠሎውም ብዙዎችን ቤት አልባ አደረገ፡፡ በዚሁ ጊዜ እኔ በቤተክርስቲያናችን ዋና ጽ/ቤት አማካኝነት ተልኬ ወደ ቦኖሻ ሄድኩ፡፡ በጊዜው የተዘጋጀው የንስሃ ፕሮግራም ነበር፡፡ በፕሮግራሙ ላይ ከጥቂት ጊዜ በፊት ሰው ጠፍቶ በኃዘን የለቀቅኩት ቅጥር ግቢ በሰው ተሞልቶ ከጸሎት ቤት አልፎ ግቢው ጠብቦት የሕዝቡም ልብ በኃዘን ተሰብሮ በንስሃ ጸሎት እምባውን ሲያፈስስ አየሁ፡፡ የጸሎት ቤቱ አቧራ የተሞላ ወለል በፈሰሰው ብዙ እምባ ርሶ አይቼ ተደነቅሁ፡፡ ከሁለት ዓመት በፊት በእምባ የለመንኩትን ልመና እግዚአብሔር መለሰልኝ፡፡ የህዝቡን ልብም እንደገና በክርስቶስ ፍቅር እንዲቀጣጠል አደረገው፡፡

ከጥቂት ጊዜ በኋላም እንደገና ትልቅ ኮንፍረንስ ተዘጋጅቶ ወደ ቦኖሻ ሄጄ ነበር፡፡ በዚያ ኮንፍረንስ ላይም ከዚያ በፊት ስጋት የነበረው የእሳት ቃጠሎ ችግር ተወግዶ ሕዝቡም ሁሉ ጌታን ለማምለክ ተጠምቶ እንደገና ግቢው ጠብቦት ተሰብስቦ ጌታን ያመልክ ነበር፡፡ ትልቅ የመልዕክት እና የወንጌል አገልግሎት ጊዜም ነበር፡፡ በዚህ ኮንፍረንስ ላይ ከ300 ሺህ ብር በላይ የስጦታ ገንዘብ ለወንጌል አገልግሎት እንዲውል ተሰበሰበ፡፡ እግዚአብሔር ጸሎቴን መለሰ፡፡

ከዚህም ሌላ በሃዲያ ሌሞ ምድር ቃልሻ በሚባለው አካባቢ አንድ ቤተ ክርስቲያን ነበረች፡፡ ይህቺ ቤተ ክርስቲያን አስቀድሞ ጥሩ መንፈሳዊ ሁኔታ ላይ የነበረች ቢሆንም በቅርቡ ግን በመሪዎች መካከል መቀባበል ጠፍቶ ክፍፍል ተፈጥሮ፤ የገንዘብ አቅሟ ተመናምኖ ለክፍለ ማኅበሩ መዋጮ የምታደርገውን ዓመታዊ 50 ብር እንኳን መክፈል አቅቷት ተዳክማ ነበር፡፡ በጊዜው የነበረው ዋና ችግር አስቀድመው የነበሩት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በእርጅና ምክንያት በሌሎች ወጣት መሪዎች ሲተኩ በሁለቱ መካከል መቀባበል መጥፋቱ ነው፡፡

እኔም ይህንን የቤተ ክርስቲያን ሁኔታ ሳይ በጣም አዘንኩ፡፡ አንድ ቀን እዚያ ቤተ ክርስቲያን ገብቼ እያለሁ እንድጸልይ እድል ሰጡኝ፡፡ እኔም የነበረው ሁኔታ በጣም አሳዝኖኝ ስለነበር በብዙ እምባ ለቤተ ክርስቲያኒቱ እና ለመሪዎቿ ጸለይኩ፡፡ ከዚያም ስለቤተ ክርስቲያኒቱ ሁኔታ አዲሶቹን መሪዎች አነጋገርኩ፡፡ እኔ ራሴ ተከታታይ ትምህርት እንዳስተምር እንዲፈቅዱ አድርጌም ራሴ ወጪዬን ችዬ እየተመላለስኩ አስተማርኳቸው፡፡ በዚሁ ጊዜም የቀድሞ መሪዎች እንዲጸልዩ እያደረግሁ የነበረው የክፍፍል መንፈስ እንዲረግብ እና መቀባበል እንዲኖር ጣርኩ፡፡ ቀስ በቀስም ትምህርቱን ስቀጥል የነበረው የተወሳሰበ ሁኔታ በሂደት እየተፈታ ሄዶ ሰላም ወረደ፡፡

እግዚአብሔር ጸሎቴን መልሶ ለክፍለ ማኅበር 50 ብር መክፈል አቅቷት ተዳክማ የነበረች ቤተ ክርስቲያን ተሻሽላ በትርፍ ጊዜ አገልጋይ ብቻ ከምትተዳደርበት ሁኔታ ወጥታ ለሁለት ወንጌላውያን የድጎማ ገንዘብ መስጠትና ስድስት መቶ ብር

እየከፈለችም አንድ ወንጌላዊ ወደ ሌላ አካባቢ ለመላክ በቃ። እኔ ከዚህ በፊት በራሴ ወጪ ስመላለስ ቆይቼ እንዳልነበር ከጥቂት ጊዜ በፊት ስሄድ ለትራንስፖርት የሚሆን ገንዘብ ሰጥተው መለሱኝ። አዲስ ትልቅ የጸሎት ቤትም ሠርተው አስመረቁ። በአገልጋዮች መካከል የነበረው ክፍፍልም ቀርቶ መቀባበል ሰፈነ።

በዚሁ ጊዜ አንድ ሽማግሌ አሁንም ልቡ አልፈታ ብሎ ከቤተ ክርስቲያን ቀርቶ ለምዕመናኑና ለራሱም ሃዘን እንደሆነ ስሰማ ቀጥ ብዬ ሰውዬው ቤት ድረስ ሄጄ በእርጋታ አነጋገርኩት። "መንግስተ ሰማያት መግባት አትፈልግም ወይ?" አልኩት። እርሱም "እፈልጋለሁ" አለ። ቀጠልኩ እናም "ታዲያ ቂመኛ መንግስተ ሰማያት አይገባም፤ እንዴት ቂም ይዘህ መንግስተ ሰማያት ልትገባ ትችላለህ?" ስለው "እኔ ይቅር ብያለሁ" ብሎ ሊከላከል ሞከረ። ጥቂት ከተነጋገርን በኋላ ግን በድንገት መንፈስ ቅዱስ ወቅሶት ከነበረበት የቅያሜ ሃሳብ ብንን በማለት ተነስቶ ቆመ። ወዲያው ተያይዘን ሄድንና የቤተ ክርስቲያን ፕሮግራም ላይ ተገኘ። የቤተ ክርስቲያኒቱ ሕዝብም በክብር ተቀብሉ ትልቅ ጋቢ አምጥቶ ሸለመው። እርቅ እና ሰላም ወረደ። እግዚአብሔር በድጋሚ የእምባ ጸሎቴን መለሰ።

ጸሎት ለአንድ አገልጋይ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ትልቅ መለኮታዊ መሣሪያ ነው። ስለዚህ አገልጋይ ሁሉ በጸሎት ሌሎችን፣ ቤተ ክርስቲያንን፣ ቤተሰቡን እና ራሱን የሚያገለግል መሆን አለበት። በእኔም ሕይወት እግዚአብሔር የጸሎትን ኃይል አለማምዶኝ በሆርኩባቸው ስፍራዎች ሁሉ ብዙ ፍሬ እንዳፈራ ረድቶኛል። ስሙ ለዘለዓለም ብሩክ ይሁን!!

# ምዕራፍ

# የታሪኩ ማስቀጠያ ምዕራፍ

## የማያረጅ ቃል ኪዳን

*ሰኔ 2003 ዓ.ም ወንጌላዊ ኬዳም ሆሳዕና አካባቢ የነበራቸውን አገልግሎት ጨርሰው ወደ አዲስ አበባ በመመለስ ላይ ነበሩ። በዚህ ጊዜ ኬዳም ከአዲሲቱ ባለቤታቸው ወ/ሮ ከበቡሽ መኮር እና መኪናውን ከሚነዳው ሹፌር ጋር በመሆን ጉዞ ቀጠሉ። ወንጌላዊው ያለ ድካም ሙሉ ቀን እየሰበኩ ማገልገል በመቻላቸው በጣም ደስታ እየተሰማቸው አገልግሎት ቀንሰው የነበረ ቢሆንም በ2003 ዓ.ም በ24 ቦታዎች ለ69 ጊዜያት ያህል መልእክት ማቅረባቸው በጣም አስደንቋቸዋል። ይህን እያወጉ በመኪና ወደ አዲስ አበባ እየተመለሱ እያለም "እግዚአብሔር 40 ዓመት ወደ ኋላ መለሰኝ" እያሉ በአድናቆት ይናገሩ ነበር።*

*ሳማሪታንስ ፐርስ የኬዳምን አገልግሎት ለማገዝ የገዛላቸው ሚትሲ ቡሺ ባለ ሁለት ጋቢና ፒክ አፕ መኪና ይዞታዋ ጥሩ ስለነበር አብርሩኝ አብርሩኝ ትላለች። ከሆሳዕና ወደ አዲስ አበባ የሚወስደው መንገድ ለመንዳት ምቹ ቢሆንም በዕለቱ የሚዘንበው ኃይለኛ ዝናብ የጉዞውን ፍጥነት የሚቀንስ ነበር። የመኪናቸው ሹፌር በዝናቡ ምክንያት ፍጥነቱን ቢገታም ምቹ መንገድ ሲያገኝ ፈጠን ብሎ መንገዱን ለማገባደድ እየጣረ ነው። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ከፊቱ በዝግታ ተላልፈው የሚሄዱ ሁለት አውቶብሶች እና አንድ የጭነት መኪናን ለመቅደም ፍጥነት ጨምሮ ሲሄድ በዝናብ የረጠበው መንገድ አንሸራቶት በግራ በኩል ያለ ቦይ ውስጥ ገባ። በጊዜው መኪናው ወደ ቦይ በገባበት በኩል ያለውን የግራ ጎማ ቦዩ ጠርዝ ላይ ያለው ድንጋይ በኃይል መቶት ነበር። ደግነቱ ቦዩ ትልቅ ስላልነበር ሹፌሩ ታግሎ መኪናዋን ወደ ኋላ ጎትቶ ከቦዩ ውስጥ አስወጣትና ጉዞአቸውን ቀጠሉ። ነገር ግን ገና ከቦዩ ወጥተው ሹፌሩ ፍጥነት ጨምሮ መሄድ እንደጀመረ ጎማው ተቀድዶ ስለነበር ተንፍሶ መሬቱን እየደበደበ ድምጽ ያሰማ ጀመረ። ሾፌሩ መኪናውን ለማቆም ሲሞክርም ከነበረው እርጥበት የተነሳ መኪናው ሊቆምለት ባለመቻሉ መንገዱን ለቅቆ በአቅራቢያው የነበረውን ቦይ ዘሎ ወደ ጉብታ ወጣ። ፍጥነት ስለነበረውም ጉብታው ላይ ሲወጣ ተገልብጦ ጎማውን ወደ ላይ ሰቀለ። በመኪናው ውስጥ የነበሩትም ከታች ሆኑ።*

-------------------------//-------------------------

በዚያ ዕለት እኔ ፍጹም በደስታ ተሞልቼ ነበር ወደ መኪናው የገባሁት። ጌታ እንዴት እንዳበረታኝ እያሰብኩ ለባለቤቴ እነግራት ነበር። በጉዞ ላይ እያለንም አንድ የተቸገረን ወንድም እያሰብኩ እኔ በምን ልረዳው እንደምችል አወጣና አወርድ ነበር። በድንገት ግን ሰይጣን ደስታዬን ሊሰርቅ አቅዶ መኪናው አደጋ አጋጠመው። በመጀመሪያ መንገድ ስቶ ሲወጣ የምንገለበጥ አልመሰለኝም ነበር። ነገር ግን መኪናው ጉብታው ላይ ወጥቶ በመጀመሪያ በጎኑ ከዚያም በጀርባው ሲተኛ እና ጎማው ወደ ላይ ሲሆን እኛም በጣም የምንጎዳና የኔም የዚህች ምድር ቆይታዬ መጨረሻ የደረሰ መስሎኝ ነበር። ሆኖም መኪናው መገለባበጡን ትቶ ከቆመ በኋላ ሁላችንም ተሯሩጠን በጎን እና በጎን ባሉት በሮች በኩል ወጣን። እራሳችንን ስናይ አንዳችንም ላይ ጭረት እንኳን አልነበረም። የመኪናው አካል የሆነው ብረት ብዙ ቦታ ተጨረማምቶ እኛ ምንም ሳንነካ ደንቆን ከባለቤቴ ጋር እልልታችንን አቀለጥነው፤ ጎምበስ ቀና እያልን እግዚአብሔርን አመሰገንን።

ዕለቱ ዝናባማም ቢሆን ሰዎች አደጋውን ሲያዩ ከያሉበት ተሯሩጠው መጡ። ሰኔ 19 ቀን ስለነበረም ገብርኤል አዳናችሁ እያሉ በመገረም አፋቸውን ያዙ። እኛም "የገብርኤል ጌታ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱም ተገኝቶ፤ ገብርኤልንም ልኮ አዳነን።" አልኳቸው። በመዝሙር ም. 18 14-15 ላይ "ኃይሌም ዝማሬዬም እግዚአብሔር ነው፤ እርሱም መድኃኒት ሆነልኝ፤ የእልልታና የመድኃኒት ድምጽ በጻድቃን ድንኳን ነው፤ የእግዚአብሔርን ክንድ አይተን እልልታ ተሞላን።" ይላል። እኔም "አልሞትም በሕይወት እኖራለሁ" ከእንግዲህም በቁጭት አገለግለዋለሁ። ምክንያቱም አሁን ሕይወታችን በአዲስ ምስጋና ተሞልቷል፤ "ከዚህ በፊት የእግዚአብሔርን ተዓምር ሰምቻለሁ። ተናግሬአለሁ። አሁን ግን እንደ ኢዮብ በአይኔ አየሁ።" አልኩኝ።

-------------------------//-------------------------

*ወንጌላዊ ኬዳም እና ባለቤታቸው በዚያ ዕለት በሕይወታቸው ባለፈው ተዓምራት እየተደነቁ በሌላ መኪና ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ። የተገለበጠችውም መኪና ወደ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ዋና ጽሕፈት ቤት ጋራዥ ተወስዳ ብዙ ወጪ ወጥቶባት ታድሳ እንደገና ኬዳምን ይዛ ለአገልግሎት መውጣቷን ቀጠለች።*

*ወንጌላዊ ኬዳምም ከእንግዲህ በቁጭት አገለግለዋለሁ እንዳሉት ላለፉት አምስት ዓመታት ያህል በቁጭት በማያረጅ ቃል ኪዳን የጠራቸውን፣ የለያቸውን፣ የጠበቃቸውንና የመራቸውን ጌታ ማገልገላቸውን በመቀጠል እንደገና በአገልግሎታቸው ብዙ ፍሬና ድል አይተዋል። በእርግጥ በሕይወታቸው ዘመን ሁሉ የነበረው የዚህ ዓለም ፈተና አሁንም ሲያደክማቸው መፈታተኑ አልቀረም። የስኳር እና የደም ብዛት ሕመማቸው በድንገት እንዳይጥላቸው በጥንቃቄ እና በቂ እረፍት በመውሰድ ለሰውነታቸው አስፈላጊ የሆነውን በመመገብ ይኖራሉ። ሆኖም ከ87 ዓመት የእድሜ*

ባለጸጋ በማይጠበቅ አቅም አሁንም ገጠር እና ከተማ ሳይመርጡ በመሃልም ሰፋ ያለ የእረፍት ጊዜ እየወሰዱም ቢሆን ራሳቸውን የሰጡትን ጌታ ያገለግላሉ። ከዚህ ጋር በተያያዘ ሲናገሩም "አሁን ለኔ ሁሉ ነገር ውድ ነው። ያለኝን እያለቀ ያለ ጊዜ፣ ያለኝን እየቀነሰ የሚሄድ ጤና፣ ያለኝን የመጨረሻ አቅም እና ብርታት አንጠፍጥፌ ጌታን አገልግዬ ወደ እረፍቴ መሄድ እፈልጋለሁ። ስለዚህም ሁሉን በጥንቃቄ አደርጋለሁ።" ይላሉ።

ከዚህም ባሻገር በርካታ የአገልግሎት አጋሮቻቸው በሞት እየተለዩአቸው በሞታቸው ቢያዝኑም በክብር እምነታቸውን ጠብቀው ወደ አምላካቸው በመሄዳቸው ግን በመደሰት ቀብረዋል። በብዙዎቹ ቀብር ላይም እየተገኙ የወንጌል መልእክት አቅርበዋል። የጌጃ ቃለ ሕይወቱ አቶ ላቀው ተሰማ፣ የኬዳሞ መንፈሳዊ አባት አባባ ሳህሌ ጆፌ፣ አባባ ሰብሮ ወሰሮ እና በቅርቡም ዶ/ር ሙላቱ ባፋ የኬዳሞ የእምነት እና የአገልግሎት አጋሮች የነበሩ እና በቅርብ ዓመታት ወደ ጌታ የተሰበሰቡ የእምነት አባቶች ናቸው።

ኬዳሞ ከዚህ በተጨማሪ የሚወዷት ሴት ልጃቸው ምህረት ኬዳሞ ልጅ በድንገተኛ አደጋ በመሞቱ የልጅ ልጅ የማጣት ኃዘንንም በእነዚሁ ዓመታት አይተዋል። በዚህ ሁሉ ፈተና ውስጥም የወንጌል አገልግሎት ፍቅር በልባቸው እየተቀጣጠለ ከእያንዳንዱ አገልግሎት በኋላ እንደገና ጌታን ማገልገል እየተጠሙ ማገልገላቸውን ቀጥለዋል።


ከዚህ የግል አገልግሎታቸው ባሻገር ባለፉት አሥር ያህል ዓመታት በግላቸው እና የቤተሰባቸው አባላት የሆኑ ልጆቻቸውን በማስተባበር ለወንጌል ሥራ ገንዘብ በማሰባሰብ ወደ ተለያዩ ስፍራዎች የሚላኩ ወንጌላውያንን ሲደጉሙ ቆይተዋል። በ2003 ዓ.ም መገባደጃ ከሆሳዕና ሲመለሱ አዋሽ ከተማ አቅራቢያ ከደረሰባቸው የመኪና መገልበጥ አደጋ የተነሳ በበለጠ ቁጭት ጌታን ለማገልገል እንደወሰኑ ሁሉ ቃላቸውን ጠብቀው ተጨማሪ ሥራ በዚያው አካባቢ መሥራት ጀምረዋል። በዚሁ መሠረትም ሁለት ወንጌላውያን ሙሉ ደመወዛቸውን በቋሚነት በመክፈል ወደ አዋሽ እንዲላኩ በማድረግ በባእድ አምልኮ ተተብትበው በስም ክርስቲያን ተብለው በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን እውነተኛውን ደህንነት ሳያገኙ ለሚኖሩት የአካባቢው የኦሮሞ ሕዝቦች ወንጌል እንዲደርስ የማድረግ አገልግሎትም በመስጠት ላይ ይገኛሉ።

ከዚህ በተጨማሪም ወንጌላዊው ለአገልግሎት በሚሄዱበት ስፍራ ሁሉ ለቤተ ክርስቲያን ከሚሰጡት አገልግሎት በማስከተል ለአገልጋዮች የምክር አገልግሎት ይሰጣሉ፤ በተጨማሪም በሄዱበት አካባቢ የሚገኙ በልዩ ልዩ ምክንያቶች ችግር ላይ ወድቀው ለሚገኙና በአገልግሎት ላይ ሆነው ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው አገልጋዮች የሚሆን ገንዘብ ይዘው በመንቀሳቀስ ለተቸገሩት መጠነኛ ድጎማ አድርገው ይመለሳሉ። ይህ ሁሉ ጥረትም የክርስቶስ ወንጌል ከነሙሉ ክብሩ እንደገና ጉዞውን በሁሉም አቅጣጫ እንዲቀጥል በማሰብ የሚደረግ ነው።


ወንጌላዊ ኬዳሞ በእርሳቸው የግል ጥረት የተጀመረው አገልጋዮችን የመደገፍ አገልግሎት በልጆቻቸው እና በአጋር የወንጌል ማኅበርተኞች ድጋፍ ቀጥሎ

ከእርሳቸውም በኋላ የወንጌሉ ዓርማ ከፍ ብሎ መውለብለቡን እንዲቀጥልና ብዙዎችም ከሰይጣን ባርነት እየወጡ የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት እንዲሆኑ ይናፍቃሉ።

ይህ መጽሐፍም እነሆ የወንጌሉ ተጋድሎ ታሪክ በአሁኑ እና በተተኪው ትውልድ ልብ እውን ሆኖ እንዲቀጥል ተጻፈ። በኬዳም የተጀመረው የወንጌል አገልጋዮችን የመደገፍ ሥራም ነገም በእርሳቸው ልጆች ና በሌሎች የወንጌል አደራን ለመወጣት በቆረጡ የክርስቶስ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ይቀጥላል። እግዚአብሔርም ብዙ ኬዳሞዎችን እንደገና አስነስቶ ወደ ነጣው የወንጌል አዝመራ ይልካል። ክብር ሁሉ ለእርሱ ይሁን!!



እግዚአብሔር ኃይሌ ነው





እኔና ደስታ ካገለገልን በኋላ






ስልጠና ከሰጠኋቸው አገልጋዮች ጋር







ስለጽናት መሸለም






ቃሉን ለመስበክ ሁሌም ዝግጁ ነበርኩ



ማስተማር




ጸሎት እና ቡራኬ



በሻሾጎ ምድር አመሻሹ ላይ ደጅ ተቀምጠን ሳለን



የማያረጀው ጠባቂዬ ከዚህም አወጣን



መኪናችን በተገለበጠበት ቦታ ላይ
ህያው ሆነን ቆመን



ስላገለገሉን እግዚአብሔር ይባርኮት



ታሪኬን የጻፈው ተመስገን ሳህለ



ከተመስገን እና የአርትኦት ሥራውን
ከሠራው ሽመልስ ኃይሌ ጋር

# የአገልግሎት አጋሮች ስለ ወንጌላዊ ኬዳሞ ምን ይላሉ

## ኬዳሞ በእምነት ከድል ወደ ድል የተሸጋገሩ ናቸው።


ወንጌላዊ ኬዳሞ ሜቻቾ በሻሸጐ ወረዳ በቢዲቃ ቀበሌ ተወልደው አድገው አባታቸው ብዙ ሃብት በእጃቸው ትተው በሞት ከዚህ ዓለም በመለየታቸው ሁለት ታላላቅ ወንድሞቻቸው ድርሻቸውን ተቀብለው ሲወጡ ገና በወጣትነታቸው እናታቸውንና እህቶቻቸውን እየረዱ የኖሩ ትጉህ ሰው ነበሩ። ከዚያም የብዙ ከብቶችና ንብረቶች ጌታ ሆነው ሳሉ ጌታ ኢየሱስን አምነው ወዲያውኑም የቃሉን እውነት ለማወቅ በመጓጓት የነበሯቸውን ከብቶች በእናታቸውና በእግዚአብሔር እጅ ትተው መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ገቡ። የፈለጉትን የቃሉን እውነት ከተረዱ በኋላ ክርስቶስን እስከ ጐልጐታ ተራራ መስቀል የወሰደውን ፍቅር እና በማቴዎስ ወንጌል 28፡18-20 ጌታ ለተከታዮቹ ያዘዘውን ትእዛዝ ከተረዱ በኋላ ወንጌላውያን ለወንጌል አገልግሎት ወደ ሲዳማ ጌዴኦ ቤተ ክርስቲያናት በወር ብር 10ና የመርፌ ቁልፍ ክፍያ ብቻ እየተሰጣቸው በሚልኩበት ዘመን ሚስዮናዊ ሆነው ሄደው ብዙ ነፍሳት በወንጌል ማርከው ቤተ ክርስቲያንን ከመሠረቱ በኋላ በባለቤታቸው ከባድ ሕመም ምክንያት ወደ ሻሸጐ ተመልሰው ለመኖር ተገደዱ። ሆኖም ይህም የእግዚአብሔር እቅድና ዓላማ ስለነበረ በቢድቃ ቅሮ ጸሎት ቤት ልጆችን ማስተማር ጀመሩ።

እኔም በበሌዣ አቶ አበበ ቡሼሮ ባሉበት ጸሎት ቤት ከምማርበት ወደ ሻሸጐ በመመለስ እርሳቸው የከፈቱት ትምህርት ቤት መጥቼ ገባሁ። ከዚያም ትምህርት የተጀመረበት ቦታ ለሻሸጐ ዳር በመሆኑ ወደ ጀሎ ጸሎት ቤት ቢወሰድ ሁሉን ያቅፋል ተብሎ ትምህርቱ በጀሎ ይካሄድ ጀመረ። ዛሬ ይህ ትምህርት ቤት ከመመስረቱ የተነሳ ለቤተ ክርስቲያን እና ለአገሪቱ የሚጠቅሙ ልጆች በእግዚአብሔር ፈቃድና በወንጌላዊ ኬዳሞ ሜቻቶ ጥረት ሊወለዱ ችለዋል።

በ3ኛ ደረጃም ኬዳሞ ለሻሸጐ ልጆች አማካይ በሚሆን ቦታ ሌላ ትምህርት ቤት ይከፈት ብለው ወደ ኡርበጫ በመሄድ የወቅቱን ባላባትና ሕዝቡን ጠርተው በማስጸደቅ ዛሬ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለመሆን የበቃውን ትምህርት ቤት እንዲከፈት አደረጉ። ትምህርት ቤቱ ሲከፈትም የቀለምና የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት አንድ ላይ ተጀምሮ በመካሄዱ እስከዛሬ ለብዙዎች የእድገት ምንጭ ሆኖ አገር አቋራጭ ወንጌላውያንና የመንግስት ኃላፊዎች የሆኑ የአገር አስተዳዳሪዎች ተወልደዋል። ይህ ሁሉ የእኚህ የወንጌል አገልጋይ የትግል


ውጤት ነው። ኬዳሞ እስከዛሬ ባላቸው አቅም ሁሉ ከዚህ ትምህርት ቤት ጐን እንደቆሙ ናቸው። ይህ በእንዲህ እንዳለ የሻሾ ቤተ ክርስቲያንን መስርተው ወደ ቦብቾ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት በመሻገር በዚያም በመምራት፣ በማደራጀትና የቃሉን እውነት ገልጸው በማስተማራቸው የከምባታና ሃዲያ ልጆች በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ሰልጥነው ወንጌላውያን እና መጋቢያን በመሆን ዛሬም ድረስ እያገለገሉ ናቸው።

ከዚያም ከሃዲያ ምድር ተለይተው ኑሮአቸውን አዲስ አበባ በማድረጋቸውም በመላው ኢትዮጵያና በዓለም ዙሪያ ሁሉ በመሄድ ጌታ የሰጣቸውን አደራ የፈጸሙ ታላቅ የወንጌል አርበኛ ለመሆን በቅተዋል። ወንጌላዊ ኬዳሞ ለአገልግሎት ራሳቸውን የሰጡ ቆራጥ የወንጌል አገልጋይ ከመሆናቸውም በላይ በጣም ታላቅ እምነት ያላቸው አባት ናቸው። እኔ እና እርሳቸው ገና የሻሾን ገጠር ቀበሌ ነዋሪዎች እያለን ወደ ቦቢቾ በመጣንበት ወቅት እኔ የአንዲት ሚሲዮናዊት ዘመናዊ ቤት አስደንቆኝ "እንደዚህ ዓይነት ቤት ውስጥ እኛ ባንኖርም የልጅ ልጆቻችን ይኖሩበታል" ብዬ ስናገር ወንጌላዊ ኬዳሞ ግን "ለምን የልጅ ልጆቻችን? እኔ ራሴ እንደዚህ ያለ ቤት ውስጥ እኖራለሁ" ብለው ተናግረው ነበር። እንደተናገሩትም በጥቂት ዓመታት ውስጥ ሻሾን የነበራቸውን የወንጌል አገልግሎት አደራ ለኔ አስረክበው የቦቢቾ ነዋሪና የግቢው ኃላፊ ሆኑ። ጥቂት ቆይተውም ወደ አዲስ አበባ ተሻገሩ። እርሳቸው እንደ እምነታቸው የተመኙት ኑሮ ሲኖሩ እኔም እንደ አለማመኔ ለዓመታት የገጠር ወንጌላዊ ሆኜ ሳገለግል ኖርኩ።



ወንጌላዊ አቡዬ ቴርካሶ

የወንጌላዊ ኬዳሞ አብሮ አደግ፣ የመጀመሪያው የወንጌላዊ ኬዳሞ ተማሪና በኋላም የሻሾንን የወንጌል አደራ ከወንጌላዊው ተረክበው ከ50 ዓመታት በላይ ወንጌልን በጽናት ያገለገሉ አባት።



## የአቶ ኬዳሞ የሕይወት ምስክርነት ...

አቶ ኬዳሞን ከ1962 ዓ.ም ጀምሮ በመጀመሪያ በትምህርትና በአገልግሎት ምክንያት ወደ አዲስ አበባ ሲመላለሱ በትንሹ አውቃቸው ነበር።

በኋላም በቅርብ ያወቅኋቸው ደግሞ ከ1966 ዓ.ም ጀምሮ በመሠረተ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ወንጌላዊ ሆነው ከመጡ በኋላ እስከ ዛሬ ድረስ በብዙ ሁኔታ ውስጥ አብረን አሳልፈን አሁንም በእግዚአብሔር ምህረትና ጸጋ አንድ ላይ አለን።

አቶ ኬዳሞ ከ1966 ዓ.ም ጀምሮ ለቤተ ክርስቲያን እድገት በር ከፋች የሆኑ አባት ናቸው። በሰንበት ትምህርትና በስብከት፣ በጉብኝት፣ ደቀ መዛሙርት በማፍራት፣ በግልና በቡድን በማስተማር፣ የደከመ በማጽናናት፣ አዲስ ወደ ጌታ የመጡትን በግልና በቡድን በማስተማር፣ በምክርና በመገሰጽ ያገለገሉ ሲሆን በቃሉ መሠረት ላይ ቆመውም ትንሽ፣ ትልቅ፣ ሴት፣ ወንድ ሳይሉ ለሁሉም በቂ ምክርና አስፈላጊ ሲሆን ተግሳጽ በመስጠት የኖሩ ጀግና አባት ናቸው። በቃልና በጸሎት በመበርታት ከሽማግሌዎች ጉባኤ አባልነት አንስቶ ሌሎችን በመምከርና ለሌሎች በመጸለይ፣ በማስተማር እና በውይይት የሚያምኑና ያንንም ተግባራዊ በማድረግ ለሌሎች ትልቅ ምስክርነት ያሳዩ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ናቸው። ለዓመታት ሳይሰለቹና ሳይደክሙ ሌሊትና ቀን በሚፈለጉበት ቦታ ሁሉ በመገኘት በቀን ከ12 ሰዓት ያላነሰ አገልግሎት እየሰጡ የኖሩ ታማኝ የወንጌል አገልጋይም ናቸው።

አቶ ኬዳሞ ጌጃ አጥቢያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ማገልገል ሲጀምሩ በአስቸጋሪ ዘመን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት በመክፈት ለቤተ ክርስቲያን ዕድገት ትልቅ በር ከፋች የሆኑ አባት ናቸው። ከጌጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን አልፈውም ለአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ጭምር ምዕመናን በቃልና በጸሎት ተግተው እንዲቆሙ ከፍተኛ ድጋፍ የሰጡ አባትም ናቸው። ይህ በትንሹ የተጀመረ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት አድጎ በሰርተፍኬት ከማስመረቅ ወደ ዲፕሎማ ከዚያም በማታና በቀን መርሃ ግብር አስተምሮ በዲግሪ የሚያስመርቅ ተቋም ወደ መሆን ተሸጋግሯል። ከዚህ እንደምንረዳው ለዚህ ትምህርት ቤት መመስረት ምክንያት የሆኑት አቶ ኬዳሞ ከፍተኛ ራዕይና ዓላማ ያላቸው አባት መሆናቸውን ነው።

ከዚህ በተጨማሪም በመንፈሳዊና በቀለም ትምህርት መስፋፋት ዙሪያ በመሥራት በማኅበረሰቡ ላይ መልካም ተጽእኖ ያመጡ አባት ናቸው። በሌላ አነጋገር የዘመናችን ሐዋርያዊ አባት ናቸው። በቃለ ሕይወት ሳይወሰኑ በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ኅብረትና በአገር አቀፍ ደረጃ በብዙ ቦታ በመንቀሳቀስ በስብከትና በማስተማር ትልቅ አስተዋጽኦ አድርገዋል፣ አሁንም በማድረግ ላይ ናቸው። ከእግዚአብሔር ጸጋ የተነሳ አቶ ኬዳሞ እግዚአብሔርን በታማኝነት፣

በትእግስትና በጽናት ያገለገሉ የቤተ ክርስቲያን አባት ናቸው። ሁልጊዜ በጸሎት፣ በትምህርት እና በምክር ከእግዚአብሔር ያገኙትን ጸጋ አገልግሎት ላይ ያውላሉ። አቶ ኬዳሞ የእግዚአብሔርን ማንነት በጥልቅ የተረዱም አባት ናቸው።

አቶ ኬዳሞ አሁንም እግዚአብሔር የሰጣቸውን ራዕይና ተልዕኮ መወጣታቸውን እንዲቀጥሉ አጥብቀን ልንጸልይላቸው ይገባናል። ዛሬ እርሳቸው በሐዋርያትና በአባቶች ዘመን ሲያገለግሉበት የነበረው የወንጌሉ ቃል ኃይል ጠንክሮ እንዲቀጥል ለጤናቸውና ለዕድሜያቸው ብሎም ለወንጌል አደራው ቀጣይነት ጽኑ ጸሎት አስፈላጊ ነው።

አቶ ኬዳሞ ብዙ ጠንካራ ጐኖች እንዳሏቸው ሁሉ ደካማ ጐኖችም አሏቸው። አቶ ኬዳሞ ደፋር፣ ቆራጥና ቁጡ ሰው ናቸው። እግዚአብሔር ግን ቅንታቸውን ተጠቅሞ ባላቸው ደካማ ጐናቸው ጭምር ለቤተ ክርስቲያን ጠቃሚ እንዲሆኑ አድርጓል። እንዳላቸው በጣም ኃይለኛ ቁጣ ቢሆን ኖሮ ብዙ ነገር ይበላሽ ነበር። ለቃሉ እውነት ከሚቀኑት ቅንዓት የተነሳም ይኸው እስከዛሬ በእርሳቸው አገልግሎት ሁሉ መልካም ሆኖ ቀጥሏል።

ደምሴ ማዴ
የቀድሞ የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን
የቦርድ ሊቀ መንበር እና ምክትል ዋና ጸሐፊ
የቀድሞ የጌጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ





# Paul and Lila Balisky's wonderful experiences with Eva. Kedamo Mechato

## 1968 to 2005

Our first acquaintance with Ato Kedamo was in 1968 when he arrived in SIM Aletta Wondo to preach at the annual Sidama KHC Conference. He arrived late in the afternoon tired and with muddy shoes because he had to walk much of the way from Bobicho to Alaba on a muddy road. At that initial meeting with Ato Kedamo our hearts were knit together in Christian love.

Ato Kedamo's preaching whether at Geja KHC or at a conference out in a KHC centre, always deeply moved us spiritually. He prepared his sermons well and spoke directly from a chapter or section of God's Word. He was not given to jumping from one text to another. We would rate him as one of the great present-day preachers of Ethiopia.

Kedamo played a crucial role in the launching of the Evangelical Theological College. Let me give some background to his role in this. In the early 1970's when Ato Kedamo was called to pastor the Geja KHC, he launched an evening Bible School in that location. During the Dergue years, 1974-1991 this evening Bible School programme gave spiritual nourishment to many of the evangelicals whose Churches were closed. Ato Kedamo asked several of us from SIM such as John Koop, Brian Farger, and me to assist in teaching. When Grace Bible Institute in Jimma was closed in 1978 by the Dergue, a KHC committee was appointed to seek ways to reopen a KHC Theological Schools in Addis Ababa. This committee was unsuccessful in their application to the Ministry of Education, now staffed by Dergue personnel. It was Ato Kedamo's strong encouragements for us just to begin teaching in the evening in the SIM HQ chapel as well as other empty rooms in the attic of the Business Department. His challenge was, "What else do you need to begin a school besides a student and a book?" As a result of Ato Kedamo's advice, the SIM Evening Bible School was launched. Under the leadership of Dr. Steve Strauss, the School grew rapidly and was renamed the Evangelical Theological College (ETC). For the record, it

is important to recognize the role that Ato Kedamo played in the initial stages of ETC.

An entire chapter could be written in Ato Kedamo's autobiography about his conference ministry as he teamed together with Mr. Albert Brant. There were no KHC centres in Southern Ethiopia where these two Godly men did not effectively preach God's word.

While Lila and were in Scotland studying for my doctorate in 1991, Ato Kedamo and Ato Markina were able to visit my home farm in Sexsmith, Alberta, Canada with Murray and Bea Coleman. These two Ethiopians arrived in winter and thus experienced our harsh Alberta weather with snow and ice. I was only sorry that I could not have been there in my home place to entertain them. They did tell me that my older brother, Ralph and his wife Jean, treated them in a wonderful manner and showed them many aspects of our life – home Church, Peace River Bible Institute, John Deere farm machinery and points of interest following their tour of N.America.

During that trip, Lila and I had the privilege of hosting Ato Kedamo along with Ato Markina in Edinburgh. They stayed several days, preaching through an interpreter at Bellevue Chapel and ministering to Ethiopian University students in Glasgow. Many were blessed by both men's ministry.

Both Lila and I have been entertained in Ato Kedamo's Addis Ababa home many times. The Kedamo family's hospitality and their evident love God's work have been an uplifting example to both Lila and me through the years.

Paul Balisky, July 21, 2013

# የአቶ ፖልና የወ/ሮ ላይላ ባልስኪ ድንቅ ገጠመኞች

# ከወንጌላዊ ኬዳሞ ሜቻቶ ጋር

# (ከ 1960 እስከ 1996 ዓ.ም)

ከወንጌላዊ ኬዳሞ ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ የተገናኘነው በሲዳማ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያናት ዓመታዊ ኮንፍራንስ ላይ ለመስበክ አለታ ወንዶ ወደሚገኘው የኤስ. አይ. ኤም ጽ/ቤት በመጣበት በ1960 ዓ.ም ነበር። ያን ዕለት ወንጌላዊ ኬዳሞ የደረሰው ዘግይቶ ከሰዓት በኋላ ሲሆን ከቦቢቾ አላባ ድረስ ያለውን አብዛኛውን ጭቃማ መንገድ በእግሩ በመጓዙ ጫማዎቹ በጭቃ ተለውሰው ነበር። ከአቶ ኬዳሞ ጋር በተገናኘንባት በመጀመሪያዋ ቅጽበት ልቦቻችን በክርስቲያናዊ ፍቅር ተሳሰሩ።

በጌጃ ቃለ ሕይወት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንም ሆነ በቃለ ሕይወት የኮንፍራንስ ማዕከላት አቶ ኬዳሞ የሚያቀርባቸው ስብከቶች ሁል ጊዜም ጥልቀት ያላቸውና መንፈሳችንን የመነቅነቅ አቅም ነበራቸው። ከተመረጠ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ቃሉን በመጥቀስ ምክሩንና ስብከቱን በተዋጣለት ሁኔታ ያቀርብ ነበር እንጂ በግብተኝነት እንዲሁ ከአንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ወደ ሌላው አይዘልም ነበር። በእኛ እምነት ዛሬም ቢሆን ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙ ምርጥ ሰባኪያን አንዱ እርሱ ነው።

ወንጌላዊ ኬዳሞ ለኢቫንጀሊካል ቴዎሎጂካል ኮሌጅ (ETC) መከፈት እጅግ ወሳኝ ሚና ተጫውቷል። ከዚህ ጋር በተያያዘ አንዳንድ ታሪካዊ ዳራዎችን ላንሳ። ወንጌላዊው ለመጋቢነት አገልግሎት ወደ ጌጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን በተጠራበት በ1962 ዓ.ም በዚያች ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በማታው ክፍለ ጊዜ ትምህርት የሚሰጠው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት እንዲከፈት አድርጓል። ከ1967-1983 ዓ.ም በዘለቀው የደርግ አገዛዝ ዘመን በርካታ አብያተ ክርስቲያናት ተዘግተው በነበረበት ወቅት ለብዙዎች መንፈሳዊ ምጋቤን በማድረግ ሲያገለግል የነበረው ይህ በማታው ክፍለ ጊዜ ይሰጥ የነበረው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ነበር። አቶ ኬዳሞ እኔን ጨምሮ ጆን ኩፕ እና ብሪያን ፋርገርን የመሳሰሉ የኤስ. አይ. ኤም አገልጋዮች በመማር ማስተማሩ ሂደት ውስጥ በመምህርነት በመሳተፍ እገዛ እንድናደርግ ይጎተጉተን ነበር። በ1970 ዓ.ም ጅማ ከተማ ይገኝ የነበረው ግሬስ (ጸጋ) የመጽሐፍ ቅዱስ ተቋም በደርግ መንግስት በተዘጋበት ወቅት እንደገና በአዲስ አበባ መከፈት የስነ መለኮት ትምህርት ቤት የሚቻልበትን ሁኔታ የሚያጠና ኮሚቴ ተዋቅሮ ሥራ ጀመረ። ታዲያ ይህ ኮሚቴ በዚያ ወቅት በትምህርት ሚኒስቴር ውስጥ በኃላፊነት ላይ ለነበሩ ሹማምንት ያቀረበው ማመልከቻ ተቀባይነትን ሳያገኝ ቀረ።

ከዚህ በኋላም አቶ ኬዳሞ እኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት እንድንጀምር ደጋግሞ በመቀስቀሱ እና በማበረታታቱ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል አካባቢ በሚገኘው የኤስ. አይ. ኤም ዋና ጽሕፈት ቤት የጸሎት ቤት አዳራሽንና ሌሎች የሥራ ክፍሎችን በመጠቀም ማስተማር ጀመርን። በዚያን ወቅት አቶ ኬዳሞ ይሞግተን የነበረው "ተማሪና መጽሐፍ ከተገኘ ትምህርት ለመጀመር ሌላ ምን ያስፈልጋል? ይህ በቂ አይደለምን?" በማለት ነበር። በዚሁ የአቶ ኬዳሞ ምክር መሰረት በኤስ. አይ. ኤም ይሰጥ የነበረው የማታው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ሊጀመር ችሏል።

ከዚህ በኋላ ትምህርት ቤቱ በዶ/ር ስቲቭ ስትራውስ አመራር እየታገዘ በአጭር ጊዜ ውስጥ ከፍተኛ እድገት ለማስመዝገብ በመቻሉ ኢቫንጀሊካል ቲዎሎጂካል ኮሌጅ (ETC) የሚል አዲስ ስያሜ አግኝቶ ሥራውን አጠናክሮ ቀጠለ። አቶ ኬዳሞ በኢቲሲ አጀማመር ላይ የተጫወተው ቁልፍ ሚና በታሪክ ተመዝግቦ ዕውቅና ሊያገኝ ይገባል።

ከዚህ ውጪ የአቶ ኬዳሞና የሚስተር አልበርት ብራንት አስደናቂ የአገልግሎት ጥምረት በራሱ አንድ ምዕራፍ ተሰጥቶት ሊጻፍ የሚችል ታሪክ ነው። ሁለቱ የወንጌል ሸክም ያላቸው የእግዚአብሔር ሰዎች በቅንጅት ደርሰው በእግሮቻቸው በመርገጥ ወንጌልን ያልሰበኩበት የደቡብ ኢትዮጵያ ክፍል የለም።

እኔ የዶክትሬት ትምህርቴን ለመቀጠል ከባለቤቴ ላይላ ጋር ወደ ስኮትላንድ አምርተን በነበረበት በ1983 ዓ.ም አቶ ኬዳሞና አቶ ማርኪና ከሚስተር ሙሬይ እና ቢይ ኮልማን ጋር በመሆን በካናዳ ሲክስሚዝ፣ አልበርታ የሚገኘውን የቤተሰባችንን እርሻ ቦታ ለመጎብኘት ችለው ነበር። እነዚህ ሁለት ኢትዮጵያውያን እዚያ የደረሱት በበረዶአማው የክረምት ወራት በመሆኑ በአስቸጋሪው የኛ አካባቢ አየር ሁኔታ እጅግ ተፈትነው ነበር። እስካሁን የሚያሳዝነኝና የሚቆጨኝ በዚያን ወቅት በትውልድ መንደሬ ላይ ሆኜ እነርሱን በእንግድነት ተቀብዬ ማስተናገድ አለመቻሌ ነው። ይሁንና በወቅቱ በስፍራው የነበረው ታላቅ ወንድሜ ራልፍ እና ባለቤቱ ጂን እጅግ አስደሳች አቀባበል እንዳደረጉላቸው ከራሳቸው አንደበት ሰምቻለሁ። በዚያን ወቅት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናችንን፣ በትውልድ መንደራችን ውስጥ የሚገኘውን የሰላም ወንዝ (Peace River)፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ተቋም፣ የጆን ዲር እርሻ ማሽነሪዎች ማምረቻንና በርካታ ነገሮችን አስጎብኝተዋቸዋል። ይህ ሁሉ እነርሱ በሰሜን አሜሪካ ያደረጉትን ጉብኝት ተከትሎ የሆነ ነበር።

በዚህ ጉብኝታቸው ወቅትም አቶ ኬዳሞና ባልንጀራቸው አቶ መርኪናን በኤድንበርግ ተቀብሎ የማስተናገዱን ዕድል አግኝተን ነበር። ለበርካታ ቀናት በነበራቸው ቆይታ በቤሌቩ ጸሎት ቤት በመገኘት በአስተርጓሚ እየተረዱ ወንጌልን ከመስበካቸውም በተጨማሪ በግላስጎው ዩኒቨርሲቲ በመማር ላይ የነበሩ ኢትዮጵያውያን

ተማሪዎችንም አገልግለዋል። በሁለቱ ሰዎች አገልግሎትም በርካታ ወገኖች ተባርከዋል።

እኔና ባለቤቴ ላይላ አዲስ አበባ በሚገኘው የወንጌላዊ ኬዳሞ የግል መኖሪያ ቤት ውስጥ በተደጋጋሚ በመጋበዝ አብረን መልካም ጊዜያትን አሳልፈናል። የኬዳሞ ቤተሰብ ያሳየን መንፈሳዊ ፍቅርና የሞቀ የወዳጅነት አቀባበል ልባችንን የሚደግፍና አርአያነት ያለው መልካም ተግባር ነው።

ፖል ባልስኪ



# ሜርል እና ጁን ዳይ "ኢትዮጵያ በነበርንባቸው ጊዜያት"

እኔና ባለቤቴ ኢትዮጵያ ውስጥ የቆየነው ከ1953 — 1964 ዓ.ም ሲሆን ደብረ ብርሃን በሚገኘው የቋንቋ ትምህርት ቤት ካገለገልን በኋላ የሀዲያ ሕዝቦች ምድር ወደሆነችው ወደ ሆሳዕና ተላክን። እዚያ የነበሩ ቀደምት ሚስዮናውያን ባደረጉት ጥረት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤትን ጨምሮ የወንዶችና የሴቶች መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች ተከፍተውና የመጻሕፍት መደብርም ተደራጅቶ ሥራ ጀምረው ነበር። እኛ ሥራ የጀመርነው በወንዶቹ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ሲሆን በኋላ ግን ለሴቶቹም ክፍት ሆኖ የአማኞችን ልጆች በስፋት ክርስቲያናዊ ትምህርት ጨምረን እናስተምር ነበር። በኋላ ላይ ግን ቤተ ክርስቲያንን በብሔራዊ ደረጃ የሚያገለግሉ መጋቢያንንና ወንጌላውያንን ለአራት ዓመታት ወደሚያሰለጥነው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ተዛውረን መሥራት ጀመርን። በዚህ መልኩ ጠንክረን እየሠራን አራት ዓመታትን በጥሩ ሁኔታ ካሳለፍን በኋላ ግን አንዳንድ መምህራን ከፍተኛ ትምህርታቸውን ለመቀጠል ሥራ እየለቀቁ በመሄዳቸው ክፍተት ተፈጥሮ ነበር።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ከሆሳዕና በ56 ኪ.ሜ ርቀት ላይ የምትገኘውና እህት ጣቢያ የሆነችው ዱራሜም የራሷ አንደኛ ደረጃ ትምህርት እና የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች ነበሯት። በዚህች ጣቢያ ትምህርታቸውን በመከታተል በብቃት አጠናቅቀው ከአገልግሎት አንጻር የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመጠባበቅ ላይ የነበሩ ጥቂት ሰዎች ነበሩ። ከእነርሱ መካከል አንዱ ወ/ዊ ኬዳሞ ሜቻቶ ነው። ስለዚህ እርሱን ፈልገን አገኘነውና ለቦቢቻው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ለቀጣዩ የትምህርት ዘመን ተጨማሪ መምህራንን እንደምንፈልግ ነገርነው። በዚያ ወቅት እኛ ወደ አገራችን ወደ አሜሪካ ለመመለስ በዝግጅት ላይ የነበርን ቢሆንም እኛን ለሚተኩት ተረኛ ሚስዮናውያን የኬዳሞን ስም በመስጠት አብሯቸው እንዲሠራ ወስነን ነበር። በዚሁ መሠረት በቀጣዩ ዓመት ኬዳሞ ቤተሰቡን ይዞ ሆሳዕና ወደሚገኘው የኤስ. አይ. ኤም ጣቢያ ጠቅልሎ በመግባት አገልግሎቱን ጀመረ። ወንጌላዊ ኬዳሞ በባህሪው እውነተኛ መሪና የአገልግሎት አጋር የነበረ፣ ይከሰቱ የነበሩ መጠነኛ አለመግባባቶችን በመፍታት የሚታወቅና በቤተ ክርስቲያናትና በጣቢያው ዘንድ በመካሪነቱ የተነገረለት አገልጋይ ነበር።

በዚህ ዘመን በአካባቢውና በዙሪያው የሚገኙ ቤተ ክርስቲያናት ወርኃዊ የሸንጎ ስብሰባ ነበራቸው። አንዳንድ ጊዜ ስብሰባዎቹ ራቅ ባሉ የኦሞ ወንዝ አቅራቢያ አካባቢዎች ይካሄዱ ስለነበር እኛና ወንጌላዊ ኬዳሞ ቀንና ማታ በመጓዝ እንሳተፍ ነበር። ኬዳሞና ባለቤቱ በርካታ የመከራና የሐዘን ገጠመኞችን በቆራጥነት እና በጽናት ያሳለፉ ሲሆን በተለይ የበኩር ልጃቸው ሞት ይጠቀሳል። ከእነርሱ ጋር

በቆየንባቸው ጊዜያት ሁሉ ኬዳሞ ለጌታ፣ ለሕዝቡ፣ ለቤተ ክርስቲያናትና ለመንግስተ ሰማይ ልዩ ፍቅር፣ አክብሮትና ናፍቆት እንደነበረው እናውቃለን።

በኋላ ላይ ግን በአገሪቱ ዋና ከተማ በአዲስ አበባ ውስጥ የምትገኝ አንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አመራሩን ለማገዝና ለመጋቢነት አገልግሎት አጥብቃ ስለፈለገችው ጥሪ አቀረበችለት። እዚህ ላይ እኔ "መልካም እድል አገኘሁ" ብሎ ባለመዝለሉ እና ፈጥኖ "እሺ" ባለማለቱ ተደንቄ ነበር። ይልቁንም ኬዳሞ በቀጥታ ወደኔ መጥቶ ነበር ጉዳዩን በእርጋታ ያማከረኝ። "እኔ ከዚህ ስሄድ በቦቢቾና በሆሳዕና ዙሪያ ሁሉ የጀመርናቸው የማስተማርና ሌሎች አገልግሎቶች ችግር እንደማይገጥማቸው እርግጠኛ መሆን እሻለሁ" ነበር ያለኝ። ሁል ጊዜም ቢሆን አንድ እርምጃ ሲወስድ ያ እርምጃ በሌሎች ላይ የሚያስከትለው ተጽዕኖ ኬዳሞን እጅግ ያስጨንቀው ነበር።

ከዚህም በተጨማሪ ደቡብን ጨምሮ በተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች በመዟዟር በታላላቅ ኮንፍራንሶች ላይ የሚያገለግል የታወቀ ሰባኪና ወደ ሌሎች ቤተ እምነቶች በተሻገረ አገልግሎቱ ትልቅ ተጽእኖ ማምጣት የቻለ የእግዚአብሔር ሰው ነው።

እኛ ከኬዳሞና ከቤተሰቡ ጋር ባለን ትውውቅ ብቻ ሳይሆን በጋራ ለእግዚአብሔር መንግስት አብረን መሥራት በመቻላችን ራሳችንን እንደ ዕድለኛ አድርገን እንቆጥራለን። ከዚህ በተጨማሪም ኬዳሞ በማስተማር እና በመምራት አገልግሎቱ እንዲቀጥል ጌታ ስለሰጠው ዕድሜና ዕድልም በጣም ደስተኞች ነን። የኬዳሞን ግለ ታሪክ የሚተርክ መጽሐፍ ታትሞ በእጃችን ቢገባ ደግሞ ደስታችን እጥፍ ድርብ ይሆናል።

ሜርል እና ጁን ዳይ

ሳሊስበሪ ኖ.ካ. አሜሪካ



## “መጽሐፉን እንደ ገጸ በረከት ይቀበሉ!”

የእግዚአብሔር ሰው ካሌብ "በብዙ የምድረ በዳ ጉዞ መንገላታት መካከል አምላኬ አሸጋግሮኝ በሕይወት አኖረኝ፤ ዛሬም ጉልበታም ነኝ" እንዳለው ሁሉ ወንጌላዊ ኬዳሞ እግዚአብሔር ለስሙ ክብር በጸጋውና በምህረቱ ጠርቶ፤ ተጠንቅቆና ጠብቆ በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ እንዲኖሩለትና እንዲያገለግሉት ዕድሜ አጥግቦ በሕይወት አኑሮአቸው ዛሬም ጉልበታም ያደረጋቸውን ሕያውና ታማኝ አምላካችን እግዚአብሔርን እጅግ በጣም አመሰግናለሁ፤ ጌታ እኮ ነው እላለሁ።

የቀዳሚው የቤተ ክርስቲያናችን ወንጌላዊ ኬዳሞ ሜቻቶ ታሪክ መጽሐፍ በቀጥታ ከአንደበታቸው የተነገረና በባለሙያ የተጻፈ በይምሰል የተጋነነ ነገር ሳይሆን ዘመናትን የዘለቀ የሕይወትና የአገልግሎት እውነተኛ ምስክርነት መጽሐፍ ነው። ወንጌላዊው ዕድሜ ልካቸውን ከወጣትነት እስከ ሽምግልና ከስልሣ ዓመታት በላይ በእግዚአብሔር ላይ በጽኑ ተደግፈው በአገልግሎት ጥሪያቸውም ጸንተውና ከቤት እስከ አደባባይ ፈታኝ ሁኔታዎችን አልፈው ከአገልግሎት ወደ አገልግሎት በማያቋርጥ ፍሬያማነት በመሸጋገር የዘለቁበትን የሕይወታቸውን አቋም ከዚህ መጽሐፍ በመመልከት ብዙ ያተርፉበታልና መጽሐፉን እንደ ገጸ በረከት ይቀበሉ።

ስለ ወንጌላዊው በዚህ አጋጣሚ ሳይጠቀስ መታለፍ የሌለበት ለቤተ ክርስቲያን መሪዎችና አገልጋዮች ሁሉ የሚጠቅም አንድ ቁም ነገር አለ። ወንጌላዊ ኬዳሞ በአገልግሎት ዘመናቸው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አልፎ አልፎ በሚፈጠር አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን አመራር ውዝግብ ወይም እሰጥ አገባ መካከል ማንንም ሳይወግኑ በአንድ የወንጌሉ እስታራቂነት አቋም የእናት ቤተ ክርስቲያናቸውን አንድነት ጠብቀውና አስጠብቀው የኖሩና የዘለቁ በመሆናቸው በቀደምት ብርቱ የእምነት አባቶች ደረጃ የሚቆጠሩ ቆራጥ አባት፤ አገልጋይና መሪ ናቸው። በአገልግሎታቸውም በሺዎችና በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ቅዱሳን ተመክረዋል፤ ተገስጸዋል፤ ተጽናንተዋል፤ የዘለዓለም ሕይወት አግኝተዋል። መጽሐፋቸውም ይህንኑ ገንቢ ወግ /ለጋሲ/ ያስቀጥላል የሚል እምነት አለኝ። ከሁሉም በላይ ደግሞ ለደካማ ኃይልን፤ ጉልበት ለሌለው ብርታትን የሚሰጠውን የእግዚአብሔርን እብሮነትና ታማኝነት ብዙዎች ያያሉ፤ ይታነጹበታልም ብዬ አምናለሁ። እንደዚሁም መልካም እረኛ፤ ስሙም ድንቅ መካር፤ ኃያል አምላክ፤ የዘላለም አባት፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ዘላለምም ለሚታመኑበት ልጆቹና አገልጋዮቹ ሁሉ ያው ነው፤ ታማኝ ነው፤ “ቅኖች ያያሉ ደስም ይላቸዋል” ተብሎ ተጽፎአልና።

ኩርሴ ሽፈዋ
የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን
ዋና ጸሐፊ

ጋሽ ኬዳሞን ከ40 ዓመታት በላይ እንዳውቃቸውና አብሬያቸው እንዳገለግል እንዲሁም በእርሳቸውና ቤተሰባቸው እኔና ቤተሰቤ መገልገል በመቻላችን ባለ ልዩ ዕድል ሆኛለሁ። ዕኚህ ሰው አንድ ሥራ አላቸው፤ ይኸውም በተገኘው ዕድል እና ሁል ጊዜ ወንጌልን ማብሰር! ጋሽ ኬዳሞ በኑሮ ወይም በህይወት፣ ሲያስተምሩ እንዲሁም በጽሑፍ አሁን ከዚህ መጽሐፋቸው እንደተረዳሁት እንደ እኛው አንድ ሰው ናቸው። በእግዚአብሔር ጸጋና ቸርነት ከመዳናቸው በስተቀር ሁለመናቸው ኃጢያተኛ የነበረ በክርስቶስ ፍቅር ተማርከ በዚያው ውስጥ በምንም አይነት ሁኔታና በማንም ልዩ ኃይል ሊወጣ በማይቻል ሁኔታ የወንጌሉ ባህር ውስጥ ተቀርቅሮ የቀረ ህይወት ያላቸው መሆኑን በሚያሳይ መልኩ የህይወት ድሎቻቸውንና ድክመቶቻቸውን ግልጥ አድርገው በዚህ መጽሐፍ አቅርበውልናል።

የረጅም ዕድሜ ልምድ በክርስቶስ ኢየሱስ መንፈስ ብቻ የተቻለን የብዙ ዓመታት አገልግሎት ቁልጭ አድርጎ ያቀረበልንን ይህን መጽሐፍ ሁላችን በማንበብ እንድንባረክ እንድንማር በዚያውም ታላቁን አምላካችንን እንድናከብር አበረታታለሁ።

ሽፈራው ወ/ሚካኤል
ለበርካታ ዓመታት የጌጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የሽማግሌዎች ጉባዔ ሰብሳቢ፣
የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተክርስቲያን ሊቀመንበር እና
የወንጌላውያን አብያተ ክርቲያናት ኅብረት ሊቀመንበር በመሆን ያገለገሉ

የአባታችን የወንጌላዊ ኬዳሞ የሕይወትና የአገልግሎት ታሪክ እግዚአብሔር የክርስቶስ አሳደጅ የነበረውን አመጸኛውን ሳውል የክርስቶስ ሐዋርያ አድርጐት በዓለም ዙሪያ ቤተ ክርስቲያን እንድትኖር፣ እንድታድግና እንድትሰፋ እንደተጠቀመበት በአዲስ ኪዳን ያነበብነው ታሪክ በእኛም ሀገር በዘመናችንና በአውዳችን እግዚአብሔር ሊደግመው እንደሚችል ያሳየን ትልቅ ማስረጃ ነው። ይህ መጽሐፍ አንድን ዐመጸኛና ትዕቢተኛ ሰው እግዚአብሔር ሊለውጠውና አገልጋዩ ሊያደርገው እንደሚችል ደግሞም አንድን አምስተኛ ክፍል ብቻ የጨረሰ ሰው ለብዙ ምሁራን መለወጥና አገልጋዮች መሆን እንዲሁም ለቀለምም ይሁን ለሥነ-መለኮት ትምህርት መስፋፋት ምክንያት አድርጐት ሊጠቀምበት እንደሚችል የሚያስተምረን ነው።

መጽሐፉ የአባባ ኬዳሞን አካላዊ ጥንካሬ፣ የአዕምሮ ብሩህነት፣ መንፈሳዊ ብቃትና የአገልግሎት ስኬት በግልጽ ያሳየናል። እግዚአብሔር የተፈጥሮ ችሎታን እና ስጦታን በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት አቃንቶ እና አስተካክሎ የጸጋ ስጦታዎቹ አካል በማድረግ መለኮታዊ ዓላማውን እንደሚፈጽምም ያስረዳናል። ነገር ግን በአባባ ኬዳሞ ሕይወትና አገልግሎት ማዕከሉ እሳቸውም ሆኑ አገልግሎታቸው ሳይሆን ክርስቶስ እንደነበረ መጽሐፉ ያሳየናል። ይህ በመሆኑም ሁሌም የዕናትና የድል፣ ከፈተና ከችግርም ነጻ የሆነ ሕይወት እንደነበራቸው መጽሐፉ አያስነብበንም። ይልቁንም በብዙ ፈተና ወስጥ እንኳ በእግዚአብሔር ቃል በመደገፋቸውና የእግዚአብሔርንም ድምፅ በተለያዩ መንገዶች ሰምተው በመታዘዛቸው ለኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስትያን ማደግና መስፋፋት ብቻ ሳይሆን በሀገራችን ለሚገኙ አብያተ ክርስቲያናትና ለዓለም ሁሉ በረከት እንዲሆኑ እግዚአብሔር እንደተጠቀመባቸው ይህ ታሪክ ይመሰክርልናል። በእርግጥም እሳቸው እንዳሉት ይህ ታሪክ የኬዳሞ ሳይሆን የእግዚአብሔር ታሪክ ነው።

ደስታ ሄሊሶ ዶ/ር

የቀድሞ የኢትዮጵያ የሥነ መለኮት ድኅረ ምረቃ ትምህርት ቤት ፕሪንሲፓል እና

የቀድሞ የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ም/ፕሬዘዳንት